# ኢትዮ ቻምበር

ሚዲያ ጭማቂ

በኢትዮጵያ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት

በኢትዮጵያ የንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የኮሚኒኬሽንና ህዝብ ግንኙነት መምሪያ የሚዘጋጅ ወርሃዊ የሚድያ ጭማቂ

ታህሳስ 2014 ዓ.ም.

ኖ ሞር ብላክ ማርኬት በሚል - 2
የንግዱ ማህበረሰብ ለዳያስፖራው - 2
የብድር ዕግድ መነሳቱ በጦርነት የተጎዳው - 3
የወተት ፋብሪካዎች በፋይናንስ እጥረትና - 3
ባንኮች ከሚያስቀምጡት መጠባበቂያ ገንዘብ -4
የጨርቃ ጨርቅና የቆዳ ኢንዱስትሪዎች -4
ማራቶን ሞተር በኤሌክትሪክ ኃይል የሚሠሩ -4
የኢትዮጵያ የውጭ ቀጥተኛ አንቨስትመንት -5
ከአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ምርት የወጪ -5
ከቡና ሻይና ቅመማ ቅመም ምርት ኤክስፖርት -5
የኢትዮጵያ ጥራት ሽልማት ድርጅት ከሜድሮክ -5
የተቀናጀ የጭነት አገልግሎት ማስተዳደሪያ -6
ብሔራዊ ባንክ የመጀመርያውን የክፍያ -6
ከ147 ነጥብ 3 ቢሊየን ብር ገቢ ተሰበሰበ -6
ከማዕድን የወጪ ንግድ 241 ሚሊየን ዶላር -6
በኢትዮጵያ መዋዕለ ንዋያቸውን ማፍሰስ -7
ሆቴሎች የብድር መክፈያ ጊዜ ለአምስት -7
የመኪና ታርጋ ለማውጣት ተቀምጦ የነበረው -7

## ምክር ቤቱ የማፅደቂያ ወርክ ሾፕ አካሄደ






የኢትዮጵያ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት "የኮቪድ-19 ወረርሽኝ በተመረጡ ዘርፎች ላይ ያሳደረው ተጽዕኖ" በሚል ርዕስ ያስጠናውን ጥናት አስመልክቶ ታህሳስ 15 ቀን 2014 ዓ.ም በራዲሰንብሉ ሆቴል የንግዱ ማህበረሰብ ተወካዮች እና ከተለያዩ ተቋማት የተውጣጡ ባለድርሻ አካላት የተሳተፉበት የማፅደቂያ ወርክ ሾፕ (Validation Workshop) አካሄደ፡፡

የወርክ ሾፑ አላማ ጠቃሚ ግብዓቶችን ከተሳታፊዎች ለማሰባሰብና የጥናቱን ሰነድ ለማዳበር ነው፡፡

የኢትዮጵያ የንግድ እና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚደንት ኢንጂነር መለአኩ እዘዘው በመድረኩ ላይ እንደገለፁት በውጪ አገር ምርቶች ላይ ጥገኛ ከመሆን ይልቅ በአምራች ዘርፉ ላይ ትኩረት በመስጠት ከውጪ የምናስገባቸውን ምርቶች በአገር ውስጥ በማምረት እና ከራስ ፍጆታ አልፎ ምርቶቹን ወደ ሌላ አገሮች በመላክ የውጪ ምንዛሬ ማስገባት ብሎም የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ማሳደግ ከሁሉም የንግዱ መሪዎች፣ ተዋናይና ከማህበረሰቡ፤ ባጠቃላይ ከግሉ ዘርፍ የሚጠበቅ ሀላፊነት ነው ብለዋል፡፡ ለወደፊቱም አገሪቱ ከኮቪድ-19 በላይ የሆኑ ችግሮች ሊያጋጥማት ስለሚችል ይህንን ጥናት እንደመነሻነት በመውሰድ በቀጣይ መፍትሄ አመንጪ የሆኑ በርካታ ጥናቶችን በማጥናትና ተግባራዊ በማድግ ችግርን ሊቋቋም የሚችል ኢኮኖሚ መገንባት አስፈላጊ እንደሆነም ፕሬዚደንቱ ጨምረው ገልፀዋል፡፡

የምክር ቤቱ ም/ዋና ፀሐፊ አቶ ውቤ መንግስቱም እንደተናገሩት የእለቱ ውይይት ውጤታማና በርካታ ጠቃሚ አስተያየቶችና ሀሳቦች የተገኙበት እንደሆነ በመግለፅ በቀጣይ ግብአቶቹ በአጥኝዎቹና በምክር ቤቱ ባለሙያዎች እየታዩ በፈርጁ በፈርጁ በሰነዱ ላይ ይካተታሉ ብለዋል፡፡

ሀገሪቱ ትኩረት በምትሰጥባቸው የአምራች ኢንዱስትሪ፣ ቱሪዝም፣ ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ እንዲሁም በግብርናው ዘርፎች ላይ የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ያስከተለው ችግሮችና መወሰድ ያለባቸው ምክረ-ሀሳቦች እነዲሁም በርካታ ነጥቦች በጥናቱ አዘጋጆች በኩል በዕለቱ ገለፃ ተደርገዋል፡፡

በጥናቱ ሰነድ ላይ በተሳታፊዎች ግልፅና ጥልቅ ውይይት ከተካሄደበት በኋላ ጠቃሚ ግብዓቶች ተሰብስበዋል፡ ሰነዱ በትሬድማርክ ኢስት አፍሪካ (Trademark East Africa) ድጋፍ አማካኝነት በኢኩማ የኮንሴልታነሲና ተሬዲንግ ሰርቪስ ኃ.የተ.የግል ድርጅት (Ekuma consultancy and Trading Service PLC) የተጠና መሆኑ ታውቋል፡፡

## አንጋፋዎቹ የኢንሹራንስ ባለሙያዎች የዕውቅናና የክብር ኒሻን ተሸለሙ

በኢትዮጵያ ኢንሹራንስ ኢንዱስትሪ ውስጥ በማገልገልና ለኢንዱስትሪው ዕድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ላበረከቱ ሁለት ጎምቱ የኢንሹራንስ ባለሙያዎች የሕይወት ዘመን አስተዋጽኦ የዕውቅናና የብር ኒሻን የክብር ሽልማት ተበረከተላቸው፡፡

ይህ የክብር ሽልማት የተበረከተላቸው አንጋፋዎቹ የኢንሹራንስ ኢንዱስትሪ ባለሙያዎች አቶ ኢየሱስ ወርቅ ዛፉና አቶ ፀጋዬ አምሲ ሲሆኑ፣ ዕውቅናውንም የሰጣቸው የኢትዮጵያ መድን ሰጪዎች ማኅበር ነው፡፡

ማኅበሩ ለሪፖርተር በላከው መረጃ፣ ሁለቱም በኢትዮጵያ ኢንሹራንስ ኢንዱስትሪ ውስጥ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረከቱ መሆናቸውን ገልጾ፣ አቶ ኢየሱስ ወርቅ ዛፉ ከ58 ዓመታት በላይ፣ አቶ ፀጋዬ አምሲ ደግሞ ከ46 ዓመታት በላይ ያገለገሉ ስለመሆናቸው አመልክቷል፡፡

ለሁለቱ ጎምቱ የኢንሹራንስ ባለሙያዎች የተበረከተውን የብር ኒሻን የክብር ሽልማት ያበረከቱላቸው የኢትዮጵያ መድን ሰጪዎች ማኅበር ፕሬዚዳንት አቶ ያሬድ ሞላ ናቸው፡፡

የዕውቅና የሽልማት ፕሮግራሙን አስመልክቶ ማኅበሩ በላከው መግለጫ፣ አቶ ኢየሱስ ወርቅ ዛፉ፣ ለባለሙያዎች ዕውቅና የሚሰጥ መርሐ ግብር ከኢንሹራንስ ኢንዱስትሪው ለረዥም ጊዜ ይጠብቁ እንደነበር ገልጸው፣ ይህንን ለመጀመርያ ጊዜ ላዘጋጁት የመድን ሰጪ ማኅበር ሥራ አስፈጻሚ አባላት ምሥጋና አቅርበዋል፡፡

አቶ ኢየሱስ ወርቅ የኢትዮጵያ የመድን ኢንዱስትሪዎች በሌሎች አገሮች እንዲገኙና የመድን ኢንዱስትሪው የራሱ የሆነና ገለልተኛ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን እንዲኖረው ለረዥም ዘመን መታገላቸውን ገልጸዋል፡፡

ጥረታቸው በመንግሥት ተቀባይነት እንዲያገኝ እንደሚገፉበትና ማኅበሩም በዚህ ጥረት መግፋት እንዳለበት አስገንዝበዋል፡፡

አቶ ፀጋዬ በበኩላቸው፣ እንዲህ ያለው ዕውቅናና ሽልማት መበረታታትና መቀጠል እንዳለበት ገልጸዋል፡፡



ዕውቅናና ሽልማት የመስጠት ጅምሩ ከታች ያሉትን ወጣት ባለሙያዎች እንደሚያበረታታና በተሻለ መልኩ ለኢንዱስትሪው ዕድገት ጉልህ አስተዋጽኦ እንደሚያበረክትም አክለዋል፡፡

የኢንሹራንስ ባለሙያዎቹ በተለይ ካለፉት 30 ዓመታት ወዲህ በኢትዮጵያ ውስጥ አንጋፋ የኢንሹራንስ ኩባንያዎች በመመሥረትና በመምራት የበለጠ የሚታወቁ ናቸው፡፡ አቶ ፀጋዬ አዋሽ ኢንሹራንስን ከምሥረታው ጥንስስ ጀምሮ በማደራጀትና ከ25 ዓመታት በላይ በዋና ሥራ አስፈጻሚነት በመምራት የዘለቁ ናቸው፡፡

አቶ ኢየሱስ ወርቅ ዛፉ ደግሞ የኅብረት ኢንሹራንስ ዋነኛ መሥራች፣ የኩባንያው ዋና ሥራ አስፈጻሚና የቦርድ ሊቀመንበር በመሆን ማገልገላቸው በዋናነት የሚጠቀስ ነው፡፡ አቶ ፀጋዬ በአዋሽ ኢንሹራንስን ከ25 ዓመታት በላይ ካገለገሉ በኋላ በክብር የተሸኙ ሲሆን፣ አቶ ኢየሱስ ወርቅ ዛፉ ደግሞ በዋናነት በኅብረት ኢንሹራስ የተመሠረተውን ኅብረት ባንክ አሁንም በቦርድ ሊቀመንበርነት እየመሩ ናቸው፡፡

ማኅበሩ እንዲህ ያለውን የዕውቅና ፕሮግራም በየዓመቱ የሚቀጥል መሆኑን አስታውቋል፡፡

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://ethiopianreporter.com/article/23929

# ኖ ሞር ብላክ ማርኬት በሚል የኢትዮጵያ ባንኮች ኤግዚቢሽን ሊካሄድ ነው

በጠቅላይ ሚኒስትር ዓብይ አህመድ (ዶ/ር) ጥሪ መሠረት እየገቡ የሚገኙ ዳያስፖራዎች ዶላራቸውን በሕጋዊ መንገድ እንዲመነዝሩ የሚያስችል የኢትዮጵያ ባንኮች ኤግዚቢሽን ማዘጋጀቱን ሰፍ ትሬዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር አስታወቀ፡፡

ማኅበሩ ታኅሳስ 20 ቀን 2014 ዓ.ም. በሰጠው መግለጫ፣ ኤግዚቢሽኑ በግሮቭ ጋርደን ዋክ ከተር 3 እስከ 5 ቀን 2014 ዓ.ም. የሚከናወን ሲሆን፣ «ኖ ሞር ብላክ ማርኬት» በሚል መሪ ቃል ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

የኤግዚቢሽኑ አዘጋጅ ወ/ሮ ኩኪ አስፋው እንደገለጹት፣ ኤግዚቢሽኑ ሕገወጥ የዶላር ምንዛሪን ለማስቀረት፣ ዳያስፖራው በአገር ውስጥ የውጭ ምንዛሪ ሒሳብ እንዲኖራቸውና ያጠራቀሙትን ገንዘብ በኢትዮጵያ ኢንቨስት ማድረግ እንዲችሉ ከባንኮች ጋር በቀጥታ የሚያገናኝ ነው፡፡

በኢትዮጵያ የሚገኙ የፋይናንስ ተቋማት በአንድ ቦታ ላይ የሚገናኙበትን መንገድ የሚፈጥር መሆኑን የገለጹት አዘጋጇ፣ ለዳያስፖራዎች በቅርበት ምርትና አገልግሎቶቻቸውን እንዲያስተዋውቁ እንዲሁም የዘመናዊ አሠራር ሒደትን እንዲከተሉ ያደርጋል ብለዋል፡፡

ባንኮች ወደ ኢትዮጵያ እየገቡ ለሚገኙ ዳያስፖራዎች የተቀላጠፈና ዘመናዊ የሆነ አገልግሎት ለመስጠት ቅድመ ዝግጅት ማጠናቀቃቸውን፣ በተለይም በአሁኑ ወቅት እየታየ ያለውን የውጭ ምንዛሪ እጥረት ለመቀነስ ታሳቢ ያደረገ መሆኑን ወ/ሮ ኩኪ አስረድተዋል፡፡

በኢትዮጵያ እየታየ ያለውን የዶላር እጥረት ለመቀነስ ያነገበ ኤግዚቢሽን እንደሆነ አክለው፣ ይኼም በሕገወጥ መንገድ የሚመነዝሩ ግለሰቦችን ቁጥር በከፊልም ቢሆን ሊቀንስ ይችላል ሲሉ አብራርተዋል፡፡

መግለጫ እስከተሰጠበት ሰዓት ድረስ 85 በመቶ የሚሆኑ ባንኮች ኤዚቢሽኑ ላይ ለመግባት ፈቃደኛ ሆነው በፊርማ ማረጋገጣቸውን፣ በቀጣይም ሌሎች ባንኮች ፈቃደኝነታቸውን ያሳያሉ ተብሎ እንደሚታሰብ አዘጋጇ አክለዋል፡፡

በኤግዚቢሽኑ ከባንኮች ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ተቋማት ጭምር የሚካፈሉበት መሆኑን፣ እነዚህም ተቋማት ምርትና አገልግሎታቸውን በአንድ ቦታ ሆነው እንዲያስተዋውቁ እንዲሁም ማኅበረሰቡ በዚህ አገራዊ ኤግዚቢሽን ላይ በመገኘት የበኩሉን ድርሻ መወጣት አለበት በማለት ጥሪያቸውን አቅርበዋል፡፡

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ አምባሳደር ዲና ሙፍቲ በበኩላቸው፣ በኢትዮጵያ ላይ የሚደረገውን ተፅዕኖ ሲቃወሙና የተለያዩ መልዕክቶችን በማኅበራዊ ሚዲያ ላይ ሲያስተጋቡ የነበሩ ዳያስፖራዎችን በመቀበል የኢትዮጵያን ህልውና ማሳደግ ይገባል ብለዋል፡፡

በተለይም «በቃ» (ኖ ሞር) የሚለው እንቅስቃሴ አገራዊ ተልዕኮ ያለበት መሆኑን የገለጹት አምባሳደሩ፣ ከዚህ ውስጥም «ኖ ሞር ብላክ ማርኬት» በሚል መሪ ቃል የሚካሄደው ኤግዚቢሽን ኢንቨስትመንትን፣ ቱሪዝምን ለማሳደግና ሌሎች ነገሮችን ለማከናወን ትልቅ ጠቀሜታ አለው ብለዋል፡፡

አንዳንድ ተቋማት ኢትዮጵያ ላይ ማዕቀብ በመጣል የውጭ ምንዛሪ እንዲቀንስ ጥረት ማድረጋቸውን፣ ይሁን እንጂ ይህንን ተፅዕኖ ለመቋቋምና ያሉትን ችግሮች ለመቅረፍ በዳያስፖራው በኩል የውጭ ከረንሲን መቀየር ተገቢ እንደሆነ አምባሳደር ዲና ተናግረዋል፡፡

ይህንንም ተልዕኮ ለማሳካት ኤግዚቢሽኑ ትልቅ አስተዋጽኦ ይኖረዋል የሚሉት አምባሳደሩ፣ የዳያስፖራውን መምጣት ተከትሎ ቀልጣፋ የሆኑ አሠራሮችን ለማካሄድ በውጭ ጉዳይ በኩል የሚመራ ኮሚቴ መዋቀሩን አብራርተዋል፡፡

ኮሚቴውም በውጭ ጉዳይ በኩል ይመራ እንጂ በጦርነቱ ምክንያት የተጎዱ ትምህርት ቤቶች፣ ሆስፒታሎች፣ መንገድና ሌሎች መሠረተ ልማቶችንና የተጎዱትን መልሶ ለማቋቋም ከተለያዩ አጋር ድርጅቶች ጋር በጋራ የሚሠራ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ዳያስፖራው ያለውን ዕውቀት፣ ክህሎትና ቴክኖሎጂ ወደ አገር ውስጥ በማምጣት እንዲሁም ደግሞ በንግድ፣ በቱሪዝምና በኢንቨስትመንቱ ላይ አሻራውን ትቶ እንዲያልፍ እየተሠራ መሆኑን የኢትዮጵያ ዳያስፖራ ኤጀንሲ የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶ ወንድወሰን ግርማ ተናግረዋል፡፡

ዳያስፖራው የውጭ ምንዛሪ ምንጭ እንዲሆን የተለያዩ አቅጣጫዎች መቀመጣቸውን ያስታወሱት ኃላፊው፣ በዳያስፖራው በኩል ከሚላከው የውጭ ምንዛሪ በሕጋዊ መንገድ የሚመነዘረው ከ30 በመቶ በታች መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በ2013 ሒሳብ ዓመት ከዳያስፖራው 3.6 ቢሊዮን ዶላር መገኘቱን፣ ከዚህ ውስጥ አንድ ሦስተኛ በታች የሚሆነው በሕጋዊ መልኩ ወደ አገር ውስጥ መግባቱን አብዛኛውን ጊዜም ሕገወጥ የሆነ ምንዛሪ እንደሚፈጸም አቶ ወንድወሰን አክለዋል፡፡

በተለያዩ አገሮች የሚገኙ ሕገወጥ የገንዘብ አዘዋዋሪዎች ኢትዮጵያ ከዳያስፖራው ማግኘት የሚገባትን ገንዘብ በቀላሉ እንዳታገኝና ላልተፈለገ ዓላማ እንዲውል እያደረጉ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

ኤጀንሲው የሕገወጥ የውጭ ምንዛሪን ለማስቆም ከዳያስፖራው ጋር ባደረገው ውይይት ላይ ከተነሱ አንኳር ነጥቦች መካከል ምንዛሪ አንድ ዓይነት ይሁን፣ ሌሎች አማራጮችን ባንኮች መዘርጋት አለባቸው የሚሉት እንደሚገኙበት ገልጸዋል፡፡

ለሕገወጥ ምንዛሪ መስፋፋት መንስዔ ከሆኑ ነገሮች መካከል አንዱ የመላኪያ ዋጋ እስከ 14 በመቶ በመሆኑ እንደሆነ፣ ይህንንም ለመቅረፍ ባንኮች እስከ 10 በመቶ ማድረግ እንደሚገባቸው ኃላፊው አስረድተዋል፡፡

በጠቅላይ ሚኒስትር ዓብይ (ዶ/ር) ጥሪ መሠረት ወደ አገር ውስጥ ለሚገቡ ዳያስፖራዎች በሕጋዊ መንገድ ምንዛሪ እንዲፈጽሙ ከአየር መንገድ ጀምሮ በተለያዩ ቦታዎች ላይ አስፈላጊው ዝግጅት መደረጉ መግለጫ በተሰጠበት ወቅት ተገልጿል፡፡

ለተጨማሪ መረጃ፡
https://ethiopianreporter.com/index.php/article/24267

# የንግዱ ማህበረሰብ ለዳያስፖራው የሚያደርገው አቀባበል

ካለፉት ሶስት ዓመታት ወዲህ በአገሪቱ የመጣውን ለውጥ ተከትሎ መንግሥት በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በአገራቸው ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ የነቃ ተሳትፎ ማድረግ እንዲችሉ ምቹ ሁኔታ ፈጥሯል። መንግሥት በሆደ ሰፊነት አሸባሪ ተብለው የተፈረደባቸውን ሳይቀር ወደ አገራቸው ገብተው በአገራቸው ጉዳይ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ዕድል በመስጠቱ በርካቶችም የዕድሉ ተጠቃሚ ሆነዋል። በፖለቲካው፣ በኢንቨስትመንት፣ በንግድና ቱሪዝም ዘርፎች በመሰማራት ራሳቸውንና አገራቸውን ለመጥቀም ያላሰለሰ ጥረት እያደረጉ ይገኛሉ። በሀገር ውስጥ ከሚያደርጉት ንቁ ተሳትፎ ባሻገር በሚኖሩበት ዓለም ሁሉ የሀገራቸው ጠበቃ በመሆን በዲፕሎማሲው መንገድ ዓለምን ያስደነገጠ ሀገርን ደግሞ ያኮራ ተግባር እየፈጸሙ ናቸው።

በተለይ አሸባሪው የትግራይ ወራሪ ቡድን ከኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች ጋር ተቀናጅቶ ኢትዮጵያን ለማፍረስ ከከፈተው ጦርነት ጎን ለጎን በምዕራባወያን መገናኛ ብዙሀን የሚያሰራጨውን ሀሰተኛ ፕሮፓጋንዳ ዲያስፖራው ማህበረሰብ በመቀልበስ የኢትዮጵያን እውነት በአንድነት በዓለም አደባባይ አስረድተዋል። ትልቁ የጦርነት ዘመቻ ለሆነው የሀሰት ፕሮፓጋንዳ ምላሽ በመስጠት ድል ማድረግ ችለዋል። ዳያስፖራው ከኢትዮጵያ አልፎ አፍሪካን በንቅናቄያቸውም ያሳተፉ ሲሆን ኢትዮጵያ የአፍሪካ ኩራት ስለመሆኗ በበርካታ አፍሪካውያን ዳግም እንዲነሳ አድርገዋል።

ምዕራባውያኑ የኢትዮጵያን እውነት በመሸፈን የሀሰት ፕሮፓጋንዳ እያራመዱ በአገሪቱ የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ በመግባት አገሪቱን ለማፈራረስ ሴራ ቢጎነጉኑም ዲያስፖራው ድርጊቱን በመቃወም የ “በቃ” ወይም “#Nomore” ዘመቻን በመላው ዓለም በማቀጣጠል ትግሉ የመላው አፍሪካ ትግል እንዲሆን አስችለዋል። በዚህም የኢትዮጵያን እውነት ለዓለም አቀፉ ማህበረሰብ በማሳየት ለአገራቸው ውድ ዋጋ ከፍለዋል።

ከዚህ ባሻገር አሸባሪው የትግራይ ወራሪ ቡድን በከፈተው ጦርነት አገሪቱ ከገባችበት የኢኮኖሚ ቀውስ እንድታገግምና በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ችግር ከመንግሥት ቁጥጥር ውጭ እንዳልሆነ ለዓለም ማህበረሰብ በማሳየት ረገድ ዳያስፖራው ማህበረሰብ የበኩሉን ሚና መወጣት እንዲችል አድርጓል። በመሆኑም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ (ዶ/ር) አንድ ሚሊዮን ዲያስፖራዎች ለገና እና ለጥምቀት በዓል ወደ አገራቸው ገብተው በጦር ግንባር የተገኘውን ድል በአገራቸው ከወገኖቻቸው ጋር በደስታ እንዲያከብሩ ጥሪ አስተላልፈዋል።

የእናት አገር ጥሪን ተቀብለው ወደ አገር ቤት እየተመሙ ያሉ ኢትዮጵያውያን፣ ትውልደ ኢትዮጵያውያን እና የኢትዮጵያ ወዳጆችም አገር ውስጥ ገብተው የሚፈጥሩት ኢኮኖሚያዊ ንቅናቄ ቀላል ግምት የሚሰጠው አይደለም። በመሆኑም በኮቪድ 19 እንዲሁም በጦርነት የተቀዛቀዘውን ኢኮኖሚ ትርጉም ባለው መንገድ ያነቃቃሉ ተብሎ ይጠበቃል።

ታዲያ ዳያስፖራው ወደ እናት አገሩ ሲገባ «ኖር» ብሎ እንደ ቤተሰብ የሚቀበለው ሕዝብ እንዳለው ማሳየት ቀዳሚ ጉዳይ መሆኑን በተለያዩ መድረኮች ተገልጿል። ለተግባራዊነቱም የትኛውም አገልግሎት ሰጪ ተቋማት አስፈላጊውን ምላሽ በአክብሮት መስጠት እንዲችሉ የንግዱ ማህበረሰብን ጨምሮ የመንግስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ከወዲሁ ቅድመ ዝግጅት እያደረጉ ስለመሆኑ ተነግሯል። ወደ አገር ቤት እየገቡ ያሉ ኢትዮጵያውያን፣ ትውልደ ኢትዮጵያውያን እና የኢትዮጵያን ወዳጆች ለመቀበል ከመንግሥት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት አንዱ የሆነው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የተቀላጠፈ አገልግሎት ለመስጠት አስፈላጊውን ዝግጅት ማድረጉን ገልጿል።

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶ አልሰን አሰፋ እንደገለጹት፤ ከቦሌ ዓለም አቀፍ አየር ማረፊያ ጀምሮ እንግዶች በሚያርፉባቸው የተለያዩ ትላልቅ ሆቴሎች ድረስ የውጭ አገር ገንዘብን መመንዘር የሚችሉ 103 ፎሬክሶች ማለትም የኤቲኤም ማሽኖች ተዘጋጅቷል። 103ቱም ፎሬክሶች ወይም የኤቲኤም ማሽኖች አስፈላጊ በሆኑ ቦታዎች ላይ የተዘጋጁ ሲሆን ዶላር ይዞ ወደ አገር ቤት የገባ አንድ ሰው ከአየር መንገድ ጀምሮ ከተዘጋጁት የኤቲኤም ማሽኖች በቀላሉ ያለምን የሰው ንክኪ ዶላሩን በመስጠት በዕለቱ ባለው የምንዛሪ ዋጋ የኢትዮጵያን ብር ማግኘት ይችላል።

ይህም ኢትዮጵያውያኑ ወደ ጥቁር ገበያ እንዳይሄዱ በማድረግ ትልቅ ሚና በመጫወት የውጭ ምንዛሪ ግኝቱን በከፍተኛ ሁኔታ ማሳደግ የሚችል ነው በማለት በኢኮኖሚው ላይ የሚያሳድረውን አዎንታዊ አስተዋጽኦ አስረድተዋል። በአዲስ አበባ ከተማ ለመዝናኛ ከተዘጋጁት አካባቢዎች በተጨማሪም በክልል ከተሞች ትላልቅ ሎጆች ባሉበት በአማራ፤ በደቡብና በኦሮሚያ ክልሎች ጭምር የውጭ ምንዛሪን ተቀብለው በብር መቀየር የሚችሉ ፎሬክሶች ወይም የኤቲኤም ማሽኖች መዘጋጀታቸውን ነው አቶ ሀልሰን የጠቆሙት።

ኢትዮጵያውያኑ ወደ አገራቸው መግባት በመቻላቸው ብቻ በጦርነቱ እንዲሁም በተለያዩ ምክንያቶች የተቀዛቀዘውን ኢኮኖሚ ማነቃቃት እንዲችሉ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የተለያዩ ሥራዎችን እየሠራ ነው። በተለይም ዳያስፖራው የተለያዩ ኢንቨስትመንቶችን ማከናወን የሚችልበት ዕድልም መፈጠሩን ጠቁመው የብድር ሁኔታዎችን ያመቻቻልም ብለዋል። በዕድሉም መኪና ቤትና መሰል ንብረቶችን መግዛት የሚፈልጉ ወደ አገር ቤት የሚገቡ ኢትዮጵያውያን ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ተበድረው መግዛት የሚችሉ መሆኑንም አስታውቀዋል።

ኢትዮጵያውያኑ ለአገር ጥሪ ምላሽ ሲሰጡ መሰል አገልግሎቶችን በተቀላጠፈ መንገድ በመስጠት አገራዊ ኃላፊነትን መወጣት ከእያንዳንዱ ዜጋ ይጠበቃል። ይሁንና አንዳንዶች የዳያስፖራውን መምጣት እንደ ጥሩ አጋጣሚ በመጠቀም ያልተገባ ትርፍ ለማግበስበስ የቋመጡ የንግድ ተቋማት እንዳሉ የተደረሰበት በመሆኑ የንግዱ ማህበረሰብ የዳያስፖራውን ወደ ሀገር ቤት መግባት መነሻ አድርጎ ከሚያደርገው የዋጋ ጭማሪ ሊታቀብ እንደሚገባ ከሰሞኑ መንግሥት አሳስቧል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሰላምና ፀጥታ ቢሮ የንግዱ ማኅበረሰብ የዳያስፖራውን ወደ ሀገር ቤት መግባት መነሻ አድርጎ ከሚያደርገው የዋጋ ጭማሪ ሊታቀብ እንደሚገባም አስታውቋል። ቢሮው ከክፍለ ከተማ አመራሮች ጋር ባደረገው ውይይት ወደ ሀገር ቤት የሚገቡ ዳያስፖራዎች ያለምንም የፀጥታ ስጋት እንዲስተናገዱ ማድረግ ተቀዳሚ ተግባሩ እንደሚሆን አመልክቷል። ሕዝቡም ከፀጥታ አካሉ ጋር ተቀናጅቶ በመሥራት ወጥ የሆነ ሕዝባዊ ዝግጅቶችን በማድረግ አጋርነቱን ማሳየት እንዳለበት ተገልጿል። በውይይት መድረኩ የጥፋት ኃይሎች አዝማሚያን በመመዘን እኩይ አላማን ማክሸፍ እንደሚያሻም የተመላከተ ሲሆን፤ በፀጥታው ኃይሉ ያላሰለሰ ጥረት እንዲሁም በማኅበረሰቡ ተሳትፎ በርካታ ወንጀሎችን መቆጣጠር መቻሉም ተነስቷል።

በአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ መርህ መሠረት አሠራሮችን መሰረት ያላደረጉ የአሠራር ክፍተቶች መስተዋላቸውም በውይይቱ የተጠቆመ ሲሆን በተለይም የንግዱ ማኅበረሰብ የትውልደ ኢትዮጵያውያን እና የኢትዮጵያ ወዳጆች ወደ ሀገር ቤት መግባታቸውን አስታኮ ከሚያደርገው የዋጋ ጭማሪ ሊታቀብ እንደሚገባ አጽንኦት ተሰጥቷል።

በተለያየ ጊዜ በአገሪቱ የሚታየው የዋጋ ግሽበት መነሻ ምክንያቱ ጤናማ የሆነ የንግድ ሥርዓት ባለመኖሩ እንደሆነ በተደጋጋሚ ባለሙያዎች ሲያነሱ ይደመጣል። የንግዱ ማህበረሰብ ምክንያታዊ ባልሆነ የዋጋ ጭማሪ የኑሮ ውድነቱን እንዳይባባስ የንግድ ሥርዓቱን ጤናማ በሆነ መንገድ መምራት እንዲቻል መንግሥትን ጨምሮ የሚመለከታቸው አካላት ተሳትፎ እንዲያደርጉም ባለሙያዎች ይመክራሉ።

በአብዛኛውም ምክንያታዊ ያልሆነ የዋጋ ጭማሪ በአገሪቱ ሲከሰት ይስተዋላል። በዚህም የኑሮ ውድነቱ መውጫ እንጂ መውረጃ ሲያገኝ አይስተዋልም። መነሻ ምክንያት የሌለው የዋጋ ጭማሪም በሕዝብ ችግር ለመጠቀም ከሚፈልጉ አንዳንድ አካላት የሚመነጭ ፍላጎት መሆኑ ይታመናል። በመሆኑም በአሁን ወቅት ወደ አገር ቤት የሚመጣውን የዳያስፖራ ማኅበረሰብ ምክንያት በማድረግ ምክንያታዊ ያልሆነ የዋጋ ጭማሪ ለማድረግ በተዘጋጁ የንግዱ ማኅበረሰብ አካላት ላይ ተጠያቂነትን እንደሚያስከትል ተገልጿል።

ከዚህ በተጨማሪም ሕገ ወጥ አካላት ላይ አስፈላጊውን ቁጥጥርና ሕግ የማስከበር ተግባር እየተከናወነ እንደሚገኝ ያመለከተው ቢሮው፤ በየአካባቢው በመሠረታዊ ፍጆታዎችና አገልግሎቶች ላይ ኢኮኖሚያዊ ምክንያት የሌለው የዋጋ ጭማሪ በሚያደርጉና ያለ አግባብ በሚያከማቹ አካላት ላይ የንግድ ቢሮዎችና የጸጥታ አካላት አስፈላጊውን እርምጃ እንዲወስዱ የታዘዙ መሆኑን ከአዲስ አበባ ፕሬስ ሴክሬታሪያት የተገኘው መረጃ አመላክቷል።

መንግሥት ለዳያስፖራው ያደረገውን ወደ አገር ቤት የጥሪ ግብዣ የተሳካ ለማድረግ በምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጪ ጉዳይ ሚኒስትር ደመቀ መኮንን የሚመራ አስተባባሪ ብሔራዊ ኮሚቴ ተዋቅሮ ወደ ሥራ መግባቱ የሚታወቅ ሲሆን፤ ኮሚቴው ዳያስፖራው ወደ አገር ቤት በሚመጣበት ወቅት ከቪዛ አሰጣጥ፣ ትራንስፖርት፣ የእንግዶች ማረፊያና ሌሎች አገልግሎት መስጫዎች ጋር በተያያዘ ምቹና ቀልጣፋ መስተንግዶ እንዲያገኙ ከማድረግ አኳያ እየተከናወኑ ባሉ ሥራዎች ላይ መምከሩም ይታወቃል።

በተጨማሪም የኢትዮጵያ አየር መንገድ፣ ኢትዮ ቴሌኮም፣ የመንግሥትና የግል ሆቴሎችና ሌሎች አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ወደ አገር ቤት ለሚመጡ ዳያስፖራዎች የዋጋ ቅናሽ እንደሚያደርጉ ማስታወቃቸውም አንደኛው ዳያስፖራው በአገር ውስጥ የሚኖረውን ቆይታ አስደሳችና ትርጉም ያለው ያደርገዋል። ለእነዚህ ኢትዮጵያውያን፣ ትውልደ ኢትዮጵያውያን እና የኢትዮጵያ ወዳጆች ወደ እናት ሀገራቸው ሲመጡ የሚሰጠው ቀልጣፋና ምቹ አገልግሎት አገርን የሚጠቅም እነሱንም የሚያከብር ሲሆን በተቃራኒው ደግሞ በዳያስፖራው ላይ ያልተገባ የዋጋ ጭማሪ ለማድረግ መሞከር ደሃውን የማሕበረሰብ ክፍል ከመጉዳት ባለፈ በአገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ የሚያሳድረው ጫና ቀላል እንደማይሆን ብዙዎች ያነሳሉ። ስለሆነም የንግዱ ማህበረሰብ ምክንያታዊ ካልሆነ የዋጋ ጭማሪ እንዲቆጠብ መንግሥት ያሳስባል።

የኢትዮጵያ ዳያስፖራ፣ በአፍሪካና በካሪቢያን የሚገኙ አድናቂዎችና በመላው ዓለም የሚኖሩ የኢትዮጵያ ወዳጆች ‘የአንድ ሚሊዮን የአገር ቤት ጉዞ ጥሪ’ ተቀብለው ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት ለኢትዮጵያ ሕዝብ ያላቸውን አጋርነት እንዲያሳዩ ጥሪ መቅረቡን ተከትሎ ኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያ ወዳጅ ዳያስፖራዎች መግባት ጀምረዋል። የእነሱ መምጣት በሀገር ኢኮኖሚ መነቃቃት ላይ የራሱ የሆነ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው ይታመናል። እነሱም በሀገራቸው ኮርተውና ተደስተው እንዲሄዱ በሁሉም መስክ መልካም አቀባበል ሊደረገላቸው ይገባል። አላስፈላጊ የዋጋ ጭማሪ ማድረግ በህግ ተጠያቂ የሚያደርግ ከመሆኑም በላይ ኢ ሞራላዊም ነው። በመሆኑም በሁሉም ዘርፍ የሚኖረው የተሳለጠ አካሄድ አንድነትን የሚያጠናክር መተሳሰብን የሚያሳድግ እንደሆን ማድረግ ያስፈልጋል። ኢትዮጵያም በውድ ልጆቿ ያላሰለሰ ጥረት የተረጋጋ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ እንቅስቃሴ በመፍጠር የጀመረችውን የብልጽግና ጉዞ ታስቀጥላለች።

ለተጨማሪ መረጃ፡
https://www.press.et/ama/?p=63296

# የብድር ዕግድ መነሳቱ በጦርነት የተጎዳው ኢኮኖሚ እንዲያገግም የሚኖረው ሚና

የኢትዮጵያ ሕዝብ “የጭን ቁስል” የሆነው አሸባሪው የሕወሓት ቡድን በትጥቅ ትግል በነበረበት 17 ዓመታት እና ሥልጣን ላይ በነበረበት 27 ዓመታት በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የፈጸመው ህልቆ መሳፍርት የሌለው ግፍና መከራ አልበቃው ብሎት፤ ከጠዋት ከማታ ሳያስበው ሥልጣኑን ከተነጠቀ ማግስት ጀምሮ የተነጠቀውን ሥልጣን ለማስመለስ አልያም ባልበላውም “ጭሬ ልበትነው” እንዳለችው እንስሳ አገሪቱን ለማፈራረስ በጋሻጃግሪዎቹ እየተመራ ወረራ፣ ዘረፋ፣ ዘር ማጥፋት፣ የኢኮኖሚ አሻጥር በጥቅሉ ሁለንተናዊ ጦርነት በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ከከፈተ ድፍን አንድ ዓመት ተቆጥሯል።

አሸባሪው ቡድን በግንባር ከከፈተው ጦርነት ጎን ለጎን የከፈተውን ‘የምጣኔ ሀብት አሻጥር’ ለመከላከል በማለም፤ በጥቁር ገበያና በመደበኛ የባንኮች የውጭ ምንዛሪ ዋጋ መካከል ያለው ልዩነት መስፋቱን ተከትሎ እንዲሁም ከዋጋ ግሽበትና ተያያዥ ነገሮች ጋር በተያያዘ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ከሐምሌ ወር ጀምሮ የብድር ክልከላ አድርጎ ነበር።

ላለፉት አራት ወራት ተግባራዊ ተደርጎ የነበረው የብድር ክልከላ ሙሉ በሙሉ መነሳቱን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ አሳውቋል። ብሔራዊ ባንክ ባንኮች ብድር እንዳይሰጡ አስተላልፎት የነበረውን መመሪያ በማንሳት፣ ለሁሉም የቢዝነስ ዘርፎች ብድር ማቅረብ እንደሚችሉ ማስታወቁ የኢኮኖሚው እንቅስቃሴ ላይ አዎንታዊ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው የምጣኔ ሃብት ምሁራንና የባንክ ባለሙያዎች ሲናገሩ ተደምጧል፡፡

ከዚህ አኳያ የብድር ክልከላው መነሳቱ በተለይ ለአገር ውስጥ ኢንቨስተሩ የሚኖረው ፋይዳ እንዲሁም የአገሪቱን የኢንቨስትመንት ዘርፍ ከማነቃቃትና በጦርነት የተጎዳውን ኢኮኖሚ እንዲያገግም በማድረግ እረገድ የሚጫወተው ሚና ምን እንደሚመስል ለዝግጅት ክፍላችን አስተያየታቸውን የሰጡት የምጣኔ ሐብት ሙህሩ አቶ ወሰንሰገድ አሰፋ፤ ላለፉት አራት ወራት ተግባራዊ ሆኖ የቆየው የብድር ክልከላ ባንኮች ላይም ሆነ የተለያዩ ቢዝነሶችና ኢንዱስትሪዎች ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳርፎ እንደነበር ጠቅሰው፣ አሁን መፈቀዱ ኢኮኖሚው ላይ መነቃቃት ይፈጥራል ብለዋል፡፡ እንደርሳቸው ገለጻ፤ የአንድ አገር ኢኮኖሚ ወይም ዓመታዊ ጥቅል ምርት (Gross Domestic Product / GDP) ሲሰላ የግል ፍጆታ (private consumption) + የግል ኢንቨስትመንት (private investment) + የመንግሥት ወጪ (Government Expenditure) + ኤክስፖርት የሚደረገው ኢምፖርት ከሚደረገው ጋር ተቀንሶ የሚገኘው የተጣራ ኤክስፖርት (Net export) ነው። ስለዚህ የአንድ አገር ጂዲፒ (የነፍስ ወከፍ ገቢ) ሲለካ እድገት አሳይቷል አልያም ዝቅተኛነው ተብሎ የሚገለጸው የነኚህ አራት መሠረታዊ ነገሮች ድምር ውጤት ነው።

ከዚህ አኳያ ከአራቱ መካከል አንዱ የሆነውን የአገሪቱን ኢንቨስትመንት ስንመለከት አብዛኛው የአገር ውስጥ ኢንቨስተሩ ከባንክ በሚያገኘው ብድር ነው ወደ ልማት ወይም ኢንቨስትመንቱ የሚገባው።

ነገር ግን የተለያዩ ንብረቶችና ገንዘቦች በአጥፊ ቡድኑ እና ተላላኪዎቹ እጅ ቢወድቅ በአገር ሉአላዊነትና በሕዝብ ህሊና ላይ ሊደርስ የሚችለውን ከባድ ችግር ቀድሞ በመረዳት እና የጥፋት ቡድኑ በአገሪቱ ላይ የተከፈተውን የኢኮኖሚ አሻጥር ለመመከት መንግሥት ባንኮች ብድር እንዳይሰጡ መመሪያ አስተላልፎ ነበር።

መንግሥት ከገንዘብ ፖሊሲ አንፃር ይህንን ዕርምጃ ሲወስድ ለአገር ኢኮኖሚ የሚጠቅሙ ሁኔታዎችን መከላከል የፈለጋቸውን ነገሮች ከመከላከል አኳያ የተወሰዱ በመሆኑ፤ ከአገራዊ ሁኔታ አንፃር ዕርምጃው በመልካም የሚታይ ነው። እንደ መንግሥት በአገሪቱ ከሚያስከትለው ቀውስ አንጻር ተገምግሞ የተወሰነም ውሳኔ ነበር።

በወቅቱ ከነበረው ሁኔታ አንፃር መንግሥት ብድር እንዲቆም ማድረጉ ትክክል ቢሆንም ቅሉ፤ በተለይ አብዛኛው የአገር ውስጥ ኢንቨስተር ወደ ኢንቨስትመንቱ የሚገባው ከባንክ ብድር አውጥቶ በመሆኑ ውሳኔው በአገሪቱ ኢንቨስትመንት ላይ አሉታዊ ተጽኖ ነበረው። ምክንያቱም ህብረተሰቡ ባንክ ላይ የቆጠበውን ገንዘብ ኢንቨስተሩ ወስዶ ሆቴል፣ ሆስፒታል፣ ሪልስቴት፣ የተቀናጀ የግብርና ሥራ ላይ ወ.ዘ.ተ የመሳሰሉ የኢንቨስትመንት ዘርፍ ላይ ገንዘቡን ፈሰስ ካላደረገ በእያንዳንዱ ሴክተር ላይ የተሰማሩ ኢንቨስተሮች እጃቸውን ለመሰብሰብ ይገደዳሉ።

ኢንቨስተሩ እጁን ለመሰብሰብ የሚገደደው ለምንድ ነው ከተባለ ኢንቨስተር ሲጀምር በራሱ ገንዘብ አይሰራም። ህብረተሰቡ የቆጠበውን ገንዘብ ከባንክ ተበድሮ ነው የሚሰራው። ስለዚህ ህብረተሰቡ የሚቆጥበውን ብር ኢንቨስተሩ ከባንክ ተበድሮ ልማት ላይ እስካላዋለው ድረስ ሥራ አይሠራም ማለት ነው።

ይህ ደግሞ ልማት ወይም ኢንቨስትመንት ቆመ ማለት ነው። ኢንቨስትመንት ተቀዛቀዘ ወይም የለም ማለት የሥራ እድል የለም ማለት ነው። የሥራ እድል ከሌለ ሰዎች ሥራ አያገኙም። የሥራ እድል ተፈጥሮለት የነበረው ዜጋ ከሥራ ገበታው የሚፈናቀልበት አጋጣሚም ይፈጠራል።

ይህ በሚሆንበት ጊዜ ፍላጎት (demand) ይወርዳል። ፍላጎት የሚጨምረው ሰዎች የሥራ እድል ተፈጥሮላቸው ገቢ ወይም ገንዘብ ሲያገኙ ነው። ለአብነት አንድ በኢንዱስትሪ ፓርክ የተቀጠረ ሠራተኛ ደመወዝ ባያገኝ ቡቲክ ገብቶ ልብስ አይገዛም። ለምግብ የሚውሉ ፍጆታዎችን ጤፍ፣ ሽንኩርት ወ.ዘ.ተ የመሳሰሉ የቤት አስቤዛዎችን አይገዛም። ምግብ ቤት ሄዶ ምግብ አይበላም።

ሻይ አይጠጣም። ስለዚህ ይህ ሰው እነዚህን መሠረታዊ ነገሮች ከማድረግ የሚቆጠብ ከሆነ፤ አምራቹ ለአብነት ምግብ አዘጋጅቶ የሚሸጥ ሰው ምግብ የሚገዛው አጥቶ በአንዴ ወደ ምግብ አለመሸጥ ከተዘዋወረ ገቢው ስለሚቀንስበት ያለው አማራጭ ሠራተኞቹን መቀነስ ሊሆን ይችላል። አሊያም ሊገዛ የነበረውን ጤፍ፣ ሥጋ ወ.ዘ.ተ ምግብ ለማዘጋጀት ግብዓት የሆኑ አቅርቦቶችን መቀነስ ሊሆን ይችላል። ይህ ሰው ሲገዛ የነበረውን የሥጋ መጠን የሚቀንስ ከሆነ ባለሥጋ ቤቱ የሚሸጠው ሥጋ ይቀንስበታል።

ባለ ሥጋ ቤቱ ሥጋውን የሚገዛው ካጣ ደግሞ ስለማያርድ የሚያርደውን በሬ ይቀንሳል ማለት ነው። ባለሥጋ ቤቱ የሚያርደውን በሬ ከቀነሰ ደግሞ በሬ ሲሸጥለት የነበረው ገበሬ በሬው ሳይሸጥለት ይቀራል ማለት ነው። ከዚህ አኳያ የአንድ ሰው ገበያ መሄድ ታች ሐረር፣ ቦረና ያለውን የበሬ ነጋዴ፤ ጎጃም ያለውን የጤፍ ነጋዴ ኢኮኖሚ ይነካል ማለት ነው። ስለዚህ ፍላጎት በመቀዝቀዙ ምክንያት ኢኮኖሚው እየወረደ ይመጣል። ሰው መግዛት ወይም ወደ ገበያ መሄድ ሳይችል ሲቀር ፍላጎት ይቀንሳል። ፍላጎት ከቀነሰ ደግሞ ከላይ የተጠቀሱት ተያያዥ ችግሮች ይከሰታሉ።

ይሄ ሁሉ የሚከሰተው ከፍላጎት መውረድ ጋር ተያይዞ እየተሰናሰነ የሚመጣ ነው። በመጀመሪያው የዓለም ጦርነት ወቅት በሰው ኪስ ገንዘብ ባለመኖሩ የፍላጎት መውረድ ተከስቶ የዓለም ኢኮኖሚ በተቀዛቀዘበት ወቅት ጆን ማይናርድ ኪንስ የተባለ የምጣኔ ሐብት ሙህር “በሰው ኪስ ገንዘብ የሚገባበትን መንገድ ማመቻቸት አለብን” የሚል ሃሳብ ይዞ ብቅ አለ። ይህንን ሃሳብ ወደ ተግባር በመለወጥ በአንደኛው የዓለም ጦርነት ወቅት ዓለም ገብታበት ከነበረው የኢኮኖሚ ቀውስ መውጣት ተቻለ። ስለዚህ ብድር መታገዱ ኢንቨስትመንቱ እንዲቀዛቀዝ ያደርገዋል።

ይህም የአንድ አገር ኢኮኖሚ ምሰሶ የሆነው ኢንቨስትመንት ተቀዛቀዘ ማለት በዛው መጠን ጂዲፒው ይወርዳል። አሁን ላይ የብድር እግዱ መነሳቱ ኢኮኖሚው እንዲነቃቃ ብቻ ሳይሆን በፋይናንስ እጥረት ቆመው የነበሩ ቢዝነሶች እና ኢንዱስትሪዎች ሥራቸውን በተሻለ እንዲሠሩ ያስችላቸዋል ያሉት የምጣኔ ሐብት ሙህሩ አቶ ወሰንሰገድ፤ ብድር ሳይኖር ሲቀር የሚያስከትለውን ችግር ከላይ አይተናል።

በተቃራኒው ደግሞ የብድር እግድ በመነሳቱ ኢንቨስትመንት ይጨምራል። የኢንቨስትመንት ፍሰት ጨመረ ማለት ዜጎች የሥራ እድል ያገኛሉ። የሥራ እድል የሚፈጠርላቸው ዜጎች ቁጥር ከጨመረ ደግሞ እያንዳንዱ ዜጋ ኪስ የሚገባው ገቢ ወይም ገንዘብ ይጨምራል። ይህም በተዘዋዋሪ ፍላጎት ይጨምራል ማለት ነው። ፍላጎት ከፍ ካለ ደግሞ ሆቴሉን ወይም የኢንቨስትመንቱን ሊዘጋ ደርሶ የነበረ ኢንቨስተር መልሶ ምርትና አገልግሎቱን ወይም ፕሮዳክሽኑን ከፍ ያደርጋል።

ስለዚህ ሰዎች ገቢ ካላቸው ፍላጎታቸው ይጨምራል። ፍላጎት ከጨመረ ደግሞ የአገሪቱን ኢኮኖሚ ከፍ የማድረግ አቅም አለው። በሌላ በኩል በተለይ የአገር ውስጥ ባለሐብቱ የቢዝነስ ሃሳብ ኖሮት ሃሳቡን ወደ ተግባር የሚያውልበት ብር ነው የሌለው። ብድሩ መለቀቁ የቢዝነስ ሃሳብ ይዘው ገንዘብ አጥተው እጃቸውን አጣጥፈው የተቀመጡ ዜጎችን ወደ ኢንቨስትመንቱ የመግባት እድላቸውን ያሰፋዋል።

እንዲሁም ብልህ ኢንቨስተሮች በራሳቸው ብር ሳይሆን በሰው ወይም በብድር ብር ነው መስራት የሚወዱት። ስለዚህ እነርሱ መንቀሳቀስ ከቻሉ አንድ ለራሳቸው ሰርተው ትርፋማ ይሆናሉ። ሁለት ደግሞ ለአገራቸው ሁለንተናዊ ኢኮኖሚ እድገት የበኩላቸውን ሚና እንዲወጡ እድል ይፈጥርላቸዋል። ሦስት በስራቸው ላሉ ዜጎች የሥራ እድል ይፈጥራሉ። መንግሥትም ከኢንቨስትመንቱ ማግኘት የሚገባውን ተገቢውን ቀረጥ ያገኛል።

ይህም የግል አልሚው፣ ተቀጣሪ ማህበረሰቡና መንግሥት በተዋረድ ተጠቃሚ ሆነው አገር ትጠቀማለች። በዚህ መንገድ ሁሉም ተጠቃሚና አሸናፊ ይሆናል። አቶ ወሰንሰገድ በኮቪድ 19 ወረርሽኝ እና በአገሪቱ ወቅታዊ ሁኔታ ሳቢያ ሕብረተሰቡ ከእለታዊ ፍጆታ ባለፈ ባንክ ላይ ያለውን ገንዘብ አውጥቶ ቢዝነስ ላይ ለማዋል እና ለመዝናናት የሚያውልበት ወቅት ባለመሆኑ የህብረተሰቡ የቁጠባ አቅም ስለሚጨምር ባንኮች ላይ ጠርቀም ያለ ገንዘብ እንደሚኖር ገልጸው፤ ባንኮች የብድር አሰጣጥ ስርዓቱን የተሳለጠና ቀልጠፋ በማድረግ መስጠት ይኖርባቸዋል።

ነገር ግን አገሪቱ የኢኮኖሚ አሻጥር ውስጥ ስላለች ብድር ተፈቅዷል በሚል ሰበብ ማንኛውም ሰው እየተበደረ ለቅንጦት እና ለእኩይ ሥራ ማስፈጸሚያነት እንዳይውል ባንኮች ብድሩን ሲሰጡ ከፍተኛ ጥንቃቄ ሊያደርጉ ይገባል።

ብድሩ ሊፈቀድ የሚገባው የአገርን ኢኮኖሚ ሊያነቃቃ፣ ዜጋን ሊጠቅምና በጦርነቱ የተዳከመውን ኢኮኖሚ ለመደገፍ በሚችል የኢንቨስትመንት ዘርፍ ለሚሰማሩ ባለሃብቶች የቅድሚያ ቅድሚያ ተሰጥቶ ብድሩ ሊፈቀድላቸው ይገባል። ስለዚህ ብድሩ ሊፈቀድ የሚገባው ኢንቨስተሩ የሥራ ፕሮፖዛሉን አቅርቦ የቀረበው ፕሮፖዛል ተገምግሞ መሆን አለበት።

በዚህ መልኩ ብድሩን በመፍቀድ ኢንቨስትመንቱ አገሪቱ ለገባችበት ቀውስ የበኩሉን አስተዋጽዖ ሊያበረክት ይገባል ብለዋል አቶ ወሰንሰገድ። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ከኢኮኖሚ አሻጥር፣ ከዋጋ ግሽበትና ተያያዥ ነገሮች ጋር በተያያዘ ባንኮች ብድር እንዳይሰጡ አስተላልፎት የነበረውን መመሪያ በማንሳት፣ ለሁሉም የቢዝነስ ዘርፎች ብድር ማቅረብ እንደሚችሉ ኅዳር 20 ቀን 2014 ዓ.ም ማስታወቁ አይዘነጋም።

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://www.press.et/ama/?p=62244

# የወተት ፋብሪካዎች በፋይናንስ እጥረትና በኢመደበኛ ንግድ ምክንያት አደጋ ውስጥ ወድቀናል አሉ

በሥራ ማስኬጃ ፋይናንስ እጥረትና የኢመደበኛ ገበያ በመስፋፋቱ የወተት ፋብሪካዎች አደጋ ላይ መውደቃቸውን ተናገሩ።

ባለፉት አምስት ዓመታት የሊዝ ፋይናንስ አቅርቦት በመስፋፋቱ ምክንያት፣ አዳዲስ የወተት ፋብሪካዎች በከፍተኛ ቁጥር ጨምሮ ከ30 በላይ ቢደርሱም፣ ለዓመታት የነበሩ ችግሮች ባለመፈታታቸው ድርጅቶቹን እየተፈታተነ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል።

በተለይም የወተት ዘርፉን የግብይት ሥርዓት የሚመራ ሕግ በአገር አቀፍ ደረጃ ባለመኖሩና በአንዳንድ ክልሎች በሥራ ላይ ያሉ መመርያዎች በሚገባ በመሬት ላይ አለመውረዳቸው፣ ከኮቪድ-19 እና ከአገሪቱ ሰላም መደፍረስ ጋር ተዳምሮ ለከፋ ቀውስ እንደዳረጋቸው የዘርፉ ተዋናዮች አስረድተዋል።

በደብረ ብርሃን ከተማ የሃፒ ወተት ፋብሪካ ባለቤትና ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ሰለሞን ፋንቱ ለሪፖርተር እንደተናገሩት፣ ወተት ከገበሬዎች መሰብሰብ ከጊዜ ወደ ጊዜ ከባድ እየሆነ መምጣቱትን በመግለጽ፣ ለዚህም ተጠያቂ ያደረጉት በኢመደበኛ ዘርፍ ያሉ ነጋዴዎችን ነው።

ፋብሪካዎች እስከ 50 ኪሎ ሜትር ዙሪያ (ራዲየስ) በመጓዝ ወተት ከገበሬዎች መግዛት ቢችሉም፣ የኢመደበኛ ገበሬዎች የተሻለ ዋጋ በመስጠት ምርቱን እየወሰዱ ፓስቸራይዝ ሳያደርጉ ይሸጣሉ ያሉት አቶ ሰለሞን፣ ይህን ዓይነት ድርጊት መፈጸም በሕግ የተከለከለ ቢሆንም፣ ሕጉ በትክክል ስለማይፈጸም ሕጋዊ አምራቾችን ከገበያ ውጭ እያደረገ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

እንደ ሾላና ማማ ወተት በሥራው ላይ የቆዩ የዘርፉ ተዋናያኖች የተሻለ የገንዘብ ፍሰት ለዓመታት ስላላቸው ችግሩን መቋቋም ቢችሉም፣ አዳዲስ ፋብሪካዎች የሥራ ማስኬጃ ካፒታል ማግኘት ባለመቻላቸው አደጋ ውስጥ መውደቃቸውን ያወሳሉ።

በዚህም የተነሳ የማምረት አቅማቸውን አሥር በመቶ እንኳን መጠቀም አለመቻላቸውን የሚያነሱት የአዳማ ወተት ፋብሪካ ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ እንዳልካቸው ንጋቱ፣ ለባለፉት ሁለት ዓመት ኪሳራ ማስመዝገባቸውን በምሬት ይናገራሉ።

የአዳማ ወተት ፋብሪካ የማምረት አቅሙ 1,500 ሊትር ወተት በሰዓት ቢሆንም፣ አሁን እያመረተ የሚገኘው በቀን 2000 ሊትር መሆኑን አቶ እንዳልካቸው ለሪፖርተር ተናግረዋል። ለዚህ በዋነኝነት ያነሱት የሥራ ማስኬጃ ካፒታል ማግኘት አለመቻላቸውን ሲሆን፣ ለዚህም ተጠያቂ ያደረጉት የኢትዮጵያ ልማት ባንክን የብድር መመርያን ነው።

«የሥራ ማስኬጃ ብድር ከባንኩ ማግኘት የማይታሰብ» ነው ያሉት አቶ እንዳልካቸው፣ ይህንንም ከሌሎች የፋይናንስ ተቋማት ለማግኘት ቢሞክሩም የብድር ታሪካቸው በመበላሸቱ ይህንን ማድረግ አለመቻላቸውን ዋና ሥራ አስኪያጁ አስረድተዋል።

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ፕሬዚዳንት ዮሐንስ አያሌው (ዶ/ር) በበኩላቸው ባንካቸው ችግሩን ለመፍታት ጥረት እያደረገ መሆኑን፣ የሥራ ማስኬጃ ካፒታል ለወተት ፋብሪካዎች ለማቅረብ መታቀዱን ይፋ አድርገዋል። ባንኩም ችግሮቻቸውን በመረዳት ማሻሻያዎችን እንደሚያደርግ ለሪፖርተር ተናግረዋል።

በኢትዮጵያ በነፍስ ወከፍ እያንዳንዱ ዜጋ በዓመት 19 ሊትር ወተት ይውስዳሉ ተብሎ የሚታመን ሲሆን፣ ከኬንያ ጋር ሲነፃፀር በስድስት እጥፍ ያነሰ ነው። በአዲስ አበባ ዙሪያ ያሉ ከ5,000 በላይ ገበሬዎች በዓመት ከ35 ሚሊዮን ሊትር በላይ ወተት ለአዲስ አበባ ገበያ ብቻ ያቀርባሉ ተብሎ ቢታመንም፣ ከዚህ ውስጥ 73 በመቶ የሚሆነው በቀጥታ ለሸማቾችና ለፋብሪካዎች ይቀርባል።

በአገር አቀፍ ደረጃ ባለፈው ዓመት 4.6 ቢሊዮን ሊትር ወተት በ57 ሺሕ ገበሬዎች መታለቡን የማዕከላዊ ስታስቲክስ አገልግሎት (የቀድሞ ማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ) መረጃ ያሳያል። ምንም እንኳን ቁጥሩ በየዓመቱ ዕድገት ቢያሳይም፣ ፋብሪካዎች ጋር ገበሬዎች ባለመቆራኘታቸው ሸማቾች ጋር የሚደርሰው አነስተኛ መሆኑ በተደጋጋሚ ይነሳል። በዚህ የተነሳ እንዲሁም በፋይናንስ እጥረትና ወተት መሰብሰብ ባለመቻላቸው፣ እንደ በቆጂ ወተት ፋብሪካ ያሉ ቀደምት ድርጅቶች በቅርቡ ተዘግተዋል፡፡

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://ethiopianreporter.com/index.php/article/24076

## ባንኮች ከሚያስቀምጡት መጠባበቂያ ገንዘብ ላይ ብድር መስጠት ጀመሩ



ባንኮች በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ከሚያስቀምጡት መጠባበቂያ ገንዘብ ላይ ለቡና ላኪዎችና አቅራቢዎች ብድር እንዲሰጡ በብሔራዊ ባንክ የተላለፈው መመርያ ከታኅሳስ 13 ቀን 2014 ዓ.ም. ጀምሮ መተግበር ጀመረ፡፡

በኢንዱስትሪው ውስጥ እስካሁን ባልተለመደ ሁኔታ ተግባራዊ እንዲሆን ከብሔራዊ ባንክ በተላለፈው መመርያ መሠረት፣ ባንኮች በብሔራዊ ባንክ ከሚያስቀምጡት የአሥር በመቶ መጠባበቂያ ገንዘብ ላይ ሁለት በመቶውን ወጪ በማድረግ ለዚሁ ዘርፍ ብድር እንደተጠቀሙበት አስታውቋል፡፡

በተለይ የቡና የወጪ ንግድ እንዳይስተጓጎል ባንኮችም የጥሬ ገንዘብ  ችግር እንዳይገጥማቸው ታሳቢ ተደርጎ ተግባራዊ እንዲሆን በተላለፈው መመርያ መሠረት፣ ለቡና ላኪዎችና አቅራቢዎች ብድር ማቅረብ ይችላሉ፡፡

ባንኮቹ ለነዚህ ዘርፎች የሚሰጡት ብድር እያንዳንዱ ባንክ ባለው መጠባበቂያ ገንዘብ ልክ መጠን የሚወሰን ነው፡፡ የተሰጠው ብድር የመመለሻ ጊዜ ገደብ የተቀመጠለት ሲሆን፣ ባንኮቹ ለነዚህ ዘርፎች የሰጡትን ብድር እስከ ነሐሴ 2014 ዓ.ም. መልሰው ወደ ብሔራዊ ባንክ  ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡

በዚህ በብሔራዊ ባንክ ሰሞናዊ ውሳኔ ላይ ካነጋገርናቸው መካከል አንዱ የሆኑት የኦሮሚያ ባንክ ፕሬዚዳንት አቶ ተፈሪ መኮንን፣ ውሳኔው ኃላፊነት የተሞላበትና ወቅቱን የጠበቀ ነው ብለዋል፡፡

አሁን ካለንበት አገራዊ ችግር አኳያ የወጪ ንግዱን ማሳደግ የግድ ነው ያሉት አቶ ተፈሪ፣ የወጪ ንግድ ደግሞ ቡና ላይ ማረፉን፣ አገራችን የተሻለ የንግድ ሚዛን እንዲኖራት ለማድረግ እንዲሁም ወቅቱ ቡና የሚገዛበትና ለውጭ ገበያ የሚዘጋጅበት እንደመሆኑ መጠን ይህንን ሊያግዝ የሚችል ውሳኔ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

የዋጋ ግሽበትን ለመቆጣጠር እየተወሰደ ካለው ዕርምጃ አኳያ ለዘርፉ ይሰጥ የነበረው የብድር አቅርቦት በጣም የመነመነ በመሆኑ በዚህ መልክ ብድር መመቻቸቱ ተገቢ መሆኑን የሚያምኑት አቶ ተፈሪ፣ በተለያዩ ምክንያቶች ባንኮች ሊገጥማቸው የሚችለውን የገንዘብ እጥረት ለመሙላትም ይረዳል ብለዋል፡፡

በተለይ በባንኮች ላይ የተጨመረው የመጠባበቂያ መጠን መጨመር፣ በአጠቃላይ ሕገወጥ የገንዘብ ዝውውርን ለመቆጣጠር በሒሳብ አከፋፈት ላይ የተወሰዱ የጥንቃቄ ዕርምጃዎች ባንኮች በቂ የብድር አቅርቦት እንዳይኖራቸው አድርጓል፡፡

በውሳኔው መሠረት ባንኮች ካላቸው መጠበቂያ ገንዘብ ለቡና ላኪዎችና አቅራቢዎች መልቀቅ መጀመራቸውንም ከአቶ ተፈሪ ገለጻ ለመረዳት ተችሏል፡፡

የሰሞኑ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ዕርምጃ አወንታዊ ሲሆን፣ ይህም ዘንድሮ ብራዚል በውርጭ ምክንያት የቡና ምርቷ ጥሩ ባለመሆኑ ለኢትዮጵያ ቡና ጥሩ ዕድል የሚከፍትና ተወዳዳሪ የሚያደርግ ይሆናል፡፡ ይህም እስከ መጋቢት ወር ድረስ እንደሚቀጥል የሚጠበቅ በመሆኑ ከዚህ ምርት የሚገኘውን የውጭ ምንዛሪ ለማሳደግ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የሰሞኑ ውሳኔ አግባብ መሆኑን ያመለክታሉ፡፡

ውሳኔው፣ ኢኮኖሚውን በማነቃቃቱ ረገድም ትልቅ ጥቅም አለው ያሉት አቶ ተፈሪ፣ ለዘርፉ የሚሰጠው ብድር ለአገር፣ ለባንክ ደንበኞች፣ ለባንኮች፣ ለገበሬውና በአጠቃላይ በቡና ግብይት ሰንሰለት ውስጥ ያሉ አካላትን በሙሉ የሚጠቅም መሆኑንም ጠቅሰዋል፡፡

ለአቅራቢው ብድር ቀርቦ ቡናው የማይሰበሰብ ከሆነ ከገበሬው ጀምሮ በአገር ደረጃ ጉዳት ሊያስከትል ይችል እንደነበርም የጠቆሙት አቶ ተፈሪ፣ ይህንን ብድር በጥንቃቄ በመስጠትና በመበደር የበኩሉን ኃላፊነት መወጣት እንዳለበትም ሳይጠቁሙ አላለፉም፡፡

ብዙ ጊዜ  ለቡና የሚሰጥ ብድር አመላለስ ላይ ችግር የሚገጥመው ከመሆኑ ጋር ተያይዞ እንዲህ ባለው መንገድ የተሰጠ ብድር በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ላይመለስ ይችላል የሚል ሥጋት ያላቸው ወገኖች ቢኖሩም፣ ወቅቱ ከቡና ሥራ ጋር የተያያዘ በመሆኑ ባንኮች በገንዘብ እጥረት ለዘርፉ የሚሰጡት ገንዘብ ካጠራቸው እንኳን በዚህ እንዲሸፍኑ መደረጉ አግባብ ነው፡፡

እንደ አንዳንድ ባንኮች የሥራ ኃላፊዎች ገለጻ፣ ለቡና ተብሎ የተሰጠው ብድር ለሌላ ዓላማ እንዳይውል ለማድረግ ጥንቃቄ የሚደረግ ሲሆን፣ በተለይ ለላኪዎች ብድሩ ሲፈቀድ  የቡና ንግድ ፈቃድ ያላቸው መሆኑ እንዲሁም ሌላ በተለይ ቡና ላኪዎቹ ቡና ለመላክ የተዋዋሉት ኮንትራት እየታየ ብድሩን በመልቀቅ ችግሩን መቅረፍ ይቻላል፡፡

ብዙ ጊዜ ግን ለቡና እየተጠሰ ያለው ብድር ለተለያዩ አገልግሎቶች ሊውል ስለሚችል አሁን አመላለሱ ላይ ችግር እንዳይገጥም ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበትም ይጠቁማሉ፡፡

የኢትዮጵያ ቡና አብቃዮች አቅራቢዎችና ላኪዎች ማኅበር ፕሬዚዳንት  ሁሴን አሞቦ (ዶ/ር) ለሪፖርተር እንደተናገሩት፣ በፋይናንስ እጥረት ምክንያት ቡና መሰብሰብ ያልተቻለ ሲሆን፣ በዚህም ምክንያት ጉዳት ሊከሰት ችሏል፡፡ ይህንን ለማስቀረት የብሔራዊ ባንክ ውሳኔ ወሳኝ ነው ያሉት ፕሬዚዳንቱ፣ በአፋጣኝ ባንኮች ብድሩን ሊለቁ እንደሚገባ ተናግረዋል፡፡

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ባንኮች በብሔራዊ ባንክ የሚያስቀምጡትን የመጠባበቂያ የገንዘብ መጠን ማሳደጉ የሚታወስ ሲሆን፣ አሁን ለነዚህ ዘርፎች የሚሰጠው ብድርም ባንኮች በብሔራዊ ባንክ ካላቸው የአሥር በመቶ መጠባበቂያ ሁለት በመቶ ያህሉን ነው፡፡

ባንኮች በአሁኑ ወቅት በብሔራዊ ባንክ አዲሱ መመርያ መሠረት ከአምስት ወደ አሥር ያደገውን የመጠባበቂያ ገንዘብ መጠን ሙሉ በሙሉ አስገብተው እንደነበር ለማወቅ ተችሏል፡፡

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://ethiopianreporter.com/index.php/article/24192

## የጨርቃ ጨርቅና የቆዳ ኢንዱስትሪዎች የውጭ ምንዛሪ ቅድሚያ እንዲያገኙ ይደረጋል ተባለ

በኢትዮጵያ በጨርቃ ጨርቅና ቆዳ ኢንዱስትሪ ዘርፍ የተሰማሩ ድርጅቶች ያሉባቸው ችግሮች እንዲቃለሉ በቅድሚያ እንዲያገኙ እንደሚደረግ ተገለጸ፡፡

ይህ የተገለጸው የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ታኅሳስ 3 ቀን 2014 ዓ.ም. በሞጆና በአዳማ ከተማ የሚገኙ የጨርቃ ጨርቅና የቆዳ ፋብሪካዎችን የሥራ እንቅስቃሴ በተጎበኘበት ወቅት ነው፡፡ ፍሬንዲሺፕ ቆዳ ፋብሪካ፣ ኮልባ ቆዳ ፋብሪካ፣ ኢቱር ቴክስታይል፣ ሰንሻይንና ኪንግደም ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካዎች የተጎበኙ ፋብሪካዎች ናቸው፡፡

የኢንዱስትሪ ሚኒስትሩ አቶ መላኩ አለበል እንደ ገለጹት፣ ኢንዱስትሪዎቹ ጥሬ ዕቃ ተጠቅመው የሚያመርቱ ስለሆኑ ድጋፍ ካገኙ ለአገር ውስጥና ለውጭ ገበያ ምርት በማቅረብ የውጭ ምንዛሪና ሰፊ የሥራ ዕድል ይፈጥራሉ፡፡

በኢንዱስትሪዎቹ ውስጥ የሚታዩና የመንግሥትን ድጋፍ የሚፈልጉ ጉዳዮች እንዳሉ በጉብኝቱ ወቅት መረዳታቸውን የገለጹት ሚኒስትሩ፣ ከእነዚህ ውስጥ አንደኛው የውጭ ምንዛሪ አቅርቦት ችግር ነው፡፡ ኢንዱስትሪዎቹ ለመለዋወጫና ለጥሬ ዕቃ የሚሆን የውጭ ምንዛሪ እንደሚፈልጉ ሚኒስትሩ አስታውቀው፣ በፍላጎታቸውም መሠረት የቅድሚያ ቅድሚያ እንዲሰጣቸው እንደጠየቁ አስረድተዋል፡፡

በሌላ በኩል ከጥሬ ዕቃ አቅርቦትና ከኮቪድ ወረርሽኝ ጋር በተገናኘ ቀደም ሲል የነበሯቸው የገበያ መዳረሻዎች ላይ መድረስ እንዳልቻሉ፣ በዚህም ምክንያት ገቢያቸው በመቀነሱ ተለዋጭ የገበያ መዳረሻ እንደሚፈልጉ ድርጅቶቹ ካቀረቧቸው ጥያቄዎች መካከል ይገኝበታል፡፡ ጥያቄዎቹ የሚመለከታቸው የመንግሥት አካላትን በማስተባበር የሚፈታ እንደሆነ የተናገሩት ሚኒስትሩ፣ በአጠቃላይ ጉብኝቱ ምን ዕድልና  ምን ችግር አለ የሚለውን የተለየበት እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

የተነሱትን ችግሮች ለኢንዱስትሪዎቹ ብቻ ሳይሆን ሌሎች ኢንዱስትሪዎችን ታሳቢ በማድረግ፣ የቅድሚያ ቅድሚያ ተሰጥቷቸው እንዲፈቱ የማድረግ ሥራ አንደኛው የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ተግባር እንደሆነ ተጠቁሟል፡፡  ኢንዱስትሪዎቹ ሥራቸው በውጭ ምንዛሪ ላይ የተመሠረተ በመሆኑ፣ ከውጭ ምንዛሪ ጋር በተገናኘ ያለውን ችግር አሁን ከሚያሳዩት አፈጻጸም ጋር ተያይዞ፣ ከብሔራዊ ባንክ ጋር በመነጋገር የሚፈታ እንደሆነ አቶ መላኩ ተናግረዋል፡፡

ከተጎበኙት ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካዎች ውስጥ ከኢትዮጵያ ልማት ባንክ ከአንድ ቢሊዮን ብር በላይ ተበድሮ ብድሩን በአግባቡ መክፈል ሳይችል በመቅረቱ፣ ባንኩ በራሱ ማስተዳደር የጀመረውና በቱርካውያን ባለቤትነት የተመሠረተው ኢቱር ቴክስታይል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ይጠቀሳል፡፡

አቶ መላኩ እንዳስታወቁት፣ በውጭ ባለሀብቶች ተይዘው የነበሩ አንዳንድ ኢንዱስትሪዎች ከብድር አመላለስ ችግር ጋር በተያያዘ በዚህ ወቅት የልማት ባንክ እያስተዳደራቸው ነው፡፡ ከእነዚህ ድርጅቶች ውስጥ ኢቱር አንደኛው ነው ያሉት አቶ መላኩ፣ ፋብሪካው የተራረፉ የጨርቃ ጨርቅ ግብዓቶችን በጥሬ ዕቃነት የሚጠቀምና ይህንንም ወደ ክርና ልብስ የሚቀይር መሆኑን አስረድተዋል፡፡ ድርጅቱ በአገሪቱ አዲስና ልዩ ተብሎ የሚወሰድ ነው ያሉት ሚኒስትሩ፣ ምናልባትም በአራትና በአምስት ዓመታት ውስጥ ሙሉ ለሙሉ ወጪውን መሸፈን የሚችል አዋጭ እንደሚሆን፣ ነገር ግን ባለሀብቶቹ የሚጠበቁባቸውን ግዴታዎች ስላልተወጡ የልማት ባንክ ተረክቦታል ብለዋል፡፡

ባንኩ ድርጅቱን ከተረከበው በኋላ ከማምረት አቅሙ በግማሽ ያህል እያመረተ መሆኑን፣ ይህም ባንኩ እስከ መጨረሻው ድረስ ፋብሪካውን ይዞ ለመቀጠል ባለው ፍላጎት መሠረት አይደለም ያሉት ሚኒስትሩ፣ ነገር ግን የፋብሪካው ሠራተኞች እንዳይበተኑ እየተመረተ ያለው ምርት ለአገርም የሚያስፈልግ እንደሆነ ታምኖበት ነው ሲሉ ገልጸዋል፡፡

‹‹በዚህ ወቅት ፋብሪካው በ50 በመቶ አቅም የሚያመርትበትን እንቅስቃሴ ወደ 75 በመቶ ከፍ እንዲያደርግ በዚህ ወቅት ከሚያስተዳድረው ማኔጅመንት ጋር ተግባብተናል፤›› ያሉት አቶ መላኩ፣ ፋብሪካውም ኤክስፖርቱን እንዲያሳድግና አዳዲስ የገበያ መዳረሻዎችን እንዲፈልግ ይደረጋል ብለዋል፡፡

አንድ ድርጅት እየሠራ ሲሸጥና ቆሞ ወይም ተዘግቶ ሲሸጥ የዋጋ ልዩነት አለው ያሉት ሚኒስትሩ፣ ፋብሪካውን ለመግዛት የሚመጡ አዳዲስ ባለሀብቶች ሠራተኞቹ ሳይበተኑ፣ የምርት ሰንሰለቱ ሳይቋረጥ ፋብሪካውን ገዝተው ወደ ሥራ የሚገቡበትን ሁኔታ ማመቻቸት ይቻላል ብለዋል፡፡

ባንኩ ድርጅቱን ለጊዜው ይዞት በጥሩ ሁኔታ እያስተዳደረው ይገኛል ያሉት አቶ መላኩ፣ ነገር ግን በዋናነት እንደሚፈለገው አዳዲስ ባለሀብቶች በሚመጡበት ጊዜ ፋብሪካው ሳይቆም ተረክበውት እንዲያስቀጥሉ እንደሚደረግ ተናግረዋል፡፡

ፋብሪካው 1,100 የሚደርሱ ሠራተኞች እንዳሉት ተገልጿል፡፡ በልማት ባንክ በኩል በጊዜያዊነት እንዲመሩት የተሾሙት ኃላፊዎች ለሚኒስትሩ እንደገለጹት፣ ፋብሪካውን ባንኩ ከተረከበ በኋላ ምንም ዓይነት ለማሽኖቹ መለዋወጫ የሚሆኑ ቁሶችን በመጋዘን አላገኙም፡፡ ማሽኖቹ የመለዋወጫ ዕቃዎች ስለሚያስፈልጋቸው የአገር ውስጥ ወኪሎችን ፈልገው እንደሚያሟሉ ተናግረዋል፡፡

ሆኖም መለዋወጫዎችን በቀጥታ ለማምጣት የባንክ ኤልሲ ለመክፈት የፋብሪካው ስም መዘዋወር ስላለበት ሒደቱን እንደ ጀመሩ ገልጸው፣ ማሽኖቹ የምርት ጊዜያቸው ትንሽ ቆየት ያለ ስለሆነ የመለዋወጫ ዕቃዎቻቸውን ማግኘት አስቸጋሪ እንደሆነባቸው አስረድተዋል፡፡

ፋብሪካውን ለመሸጥ በመስከረምና በጥቅምት ወራት ጨረታ እንደወጣ የተገለጸ ሲሆን፣ ግምቱ ወደ 1.4 ቢሊዮን ብር በመሆኑ በጨረታው ሊወዳደር የፈለገ ባለሀብት እንዳልቀረበ ተገልጿል፡፡

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://ethiopianreporter.com/index.php/article/24078

## ማራቶን ሞተር በኤሌክትሪክ ኃይል የሚሠሩ ተሽከርከሪዎች ቻርጅ የሚደርጉበትን ማዕከል አስመረቀ

በታዳሽ ኃይል የሚሠሩ የተለያዩ የሐንዳይ ተሽርካሪዎችን በኢትዮጵያ በብቸኝነት የሚገጣጥመው ማራቶን ሞተር ኢንጂነሪንግ፣ 20 በታዳሽ ኃይል የሚሠሩ ተሽከርካሪዎችንና ቻርጅ የሚደረጉበትን ማዕከል ታኅሳስ 19 ቀን 2014 ዓ.ም. በይፋ አስመረቀ፡፡

የማራቶን ሞተር ኢንጂነሪንግ መሥራችና ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ መልካሙ አሰፋ እንዳስታወቁት፣ ድርጅቱ ሁለት የተለያየ የሐዩንዳይ ሞዴል የሆኑ ሃያ በኤሌክትሪክ የሚሠሩ ተሽከርከሪዎችን ገጣጥሞ ለአገልግሎት አቅርቧል፡፡ የመጀመርያው ሞዴል ሐንዳይ ኮና ሲባል ሌላኛው ደግሞ ሐንዳይ ኮኒክ ይባላል፡፡ ድርጅቱ ከዚህ በተጨማሪም ከመኪኖቹ መገጣጠም እኩል አስፈላጊ የሆነውን መሠረተ ልማት ወይም የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ ቻርጅ ማዕከል በ30 ሺሕ ካሬ ሜትር ላይ ባረፈው ፋብሪካው ውስጥ ገንብቷል፡፡

የድርጅቱ ዓላማ በኤሌክትሪክ የሚሠራ ተሽከርካሪን ማስተዋወቅ ብቻ አይደለም ያሉት አቶ መልካሙ፣ ለዚያ የሚሆነውን መሠረተ ልማት መገንባት ሌላው ዕቅዱ ነው ብለዋል፡፡

ማራቶን ሞተርስ አሥር ሺሕ መኪኖችን በዓመት የማምረት አቅም እንዳለው፣  ለመጀመርያ ጊዜ በ2011 ዓ.ም. ከገጣጠመው ተሽከርካሪ በኋላ 20 በኤሌክትሪክ የሚሠሩ መኪኖች ለመግጠም እንደበቃ ተገልጿል፡፡

ኢትዮጵያ በየዓመቱ ለነዳጅ ግዥ የሚውል እስከ 2.5 ቢሊዮን ዶላር ታወጣለች፡፡

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://ethiopianreporter.com/index.php/
article/24224

## የኢትዮጵያ የውጭ ቀጥተኛ አንቨስትመንት ቢያሽቆለቁልም የኢኮኖሚ ዕድገቱ ግን አዎንታዊ መሆኑ ተገለጸ



ዓለም አቀፉ የኢኮኖሚና ፋይናንስ ግምገማ ተቋም ኧርነስት ኤንድ ያንግ (Ernst and Young) እ.ኤ.አ. 2021 ባቀረበው የአፍሪካ የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት ሪፖርት "Africa Attractiveness Report 2021" መሠረት፣ የምሥራቅ አፍሪካ ቀጣና ዝቅተኛ የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት የሳበ ተብሏል፡፡

የቀጣናው የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት ያሽቆለቆለው በኢትዮጵያ በተፈጠረው የፖለቲካ አለመረጋጋት ምክንያት እንደሆነ ሪፖርቱ ይገልጻል፡፡

የኢትዮጵያ የመንግሥት ኮሙዩኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር ደኤታ ሰላማዊት ካሳ ታኅሳስ 4 ቀን 2014 ዓ.ም. በሰጡት መግለጫ፣ በ2014 በጀት ዓመት ባለፉት ሦስት ወራት የነበረው የአገሪቱ የኢኮኖሚ አፈጻጸም መልካም ውጤትና ዕድገት የታየበት መሆኑን አመልክተው ነበር፡፡

በሩብ ዓመቱ የአገሪቱ የዋጋ ግሽበት መቀነስ የታየበት መሆኑን፣ የወጪ ንግድ (ኤክስፖርት) ገቢ መጨመሩን፣ እንዲሁም የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ፍሰት ማደጉንና የአገር ውስጥ ታክስ ገቢም መሻሻሉን ገልጸዋል፡፡

ዓምና በተመሳሳይ ሦስት ወራት ከተመዘገበው በ10.8 በመቶ ያደገ የታክስ ገቢ ዘንድሮ በሦስት ወራት መሰብሰቡን፣ በኤክስፖርት ንግድ ረገድም 16 በመቶ ብልጫ ያለው 972 ሚሊዮን ዶላር ገቢ መገኘቱን ያስረዱት ሚኒስትር ደኤታዋ፣ የዋጋ ግሽበት መረጋጋቱንና የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትም ማደጉን በዋናነት ገልጸዋል፡፡

የኢትዮጵያ መንግሥት ይህን ቢልም የምሥራቅ አፍሪካ ቀጣና፣ እንዲሁም የኢትዮጵያ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ፍሰት ዘንድሮ ማሽቆልቆሉን ነው የኧርነስት ኤንድ ያንግ ሪፖርት ያመለከተው፡፡ በኮሮና ወረርሽኝ የተነሳ ክፉኛ የተጎዳው የአፍሪካ ኢኮኖሚ እ.ኤ.አ. በ2020 የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ፍሰቱ 50 በመቶ መውረዱን ሪፖርቱ አመልክቷል፡፡

ይህ ደግሞ አፍሪካን በወረርሽኙ ክፉኛ የደቀቀች አኅጉር ያደረጋት ሲሆን፣ የአኅጉሩ ጥቅል ኢኮኖሚ (ጂዲፒ) ወደ 2.4 በመቶ መኮማተሩንም ይገልጻል፡፡ ሆኖም በማዕድን ዘርፍ ዕድገት ታግዞ ኢኮኖሚው እ.ኤ.አ. በ2021 መጠነኛ መነቃቃት በማሳየት ወደ አራት በመቶ ከፍ እንደሚል ያመለከተው ሪፖርቱ፣ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትና አጠቃላይ ዕድገቱም አንፃራዊ መሻሻል እንደሚታይበት ነው የተነበየው፡፡

የአፍሪካ ቴሌኮም ዘርፍ ከፍተኛ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ፍሰት ያገኘ መሆኑን ሪፖርቱ ይገልጻል፡፡ በአጠቃላይ በዓመቱ ናይጄሪያ 6.6 ቢሊዮን ዶላር የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት በመሳብ አንደኛ ስትሆን፣ ደቡብ አፍሪካ 3.8 ቢሊዮን ዶላር፣ አንጎላ 3.1 ቢሊዮን ዶላር እንዲሁም ሞሮኮ 2.4 ቢሊዮን ዶላር ኢንቨስትመንት ከውጭ በመሳብ ይከተሏታል ተብሏል፡፡

የምሥራቅ አፍሪካ ቀጣና የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት በፀጥታ ችግርና በፖለቲካ አለመረጋጋት ቀንሷል ቢልም ሪፖርቱ፣ በአጠቃላይ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ፍሰቱም ሆነ የኢኮኖሚ ዕድገቱ አዎንታዊ ሆኖ እንደሚቀጥል ተገልጿል፡፡ እንደ ኬንያ፣ ኢትዮጵያና ታንዛኒያ ባሉ የቀጣናው አገሮች የኢኮኖሚ ዕድገትም ሆነ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ቅናሽ ቢታይባቸውም ኢኮኖሚው ግን ጤናማ ሆኖ ይቀጥላል ይላል ሲል ሪፖርቱ አስረድቷል፡፡

ለተጨማሪ መረጃ፡
https://ethiopianreporter.com/index.php/article/24079

## ከቡና ሻይና ቅመማ ቅመም ምርት ኤክስፖርት ከ525 ሚሊየን የአሜሪካ ዶላር በላይ ገቢ ተገኘ

በበጀት ዓመቱ አምስት ወራት ከቡና ሻይና ቅመማ ቅመም ምርት ኤክስፖርት 525 ነጥብ 6 ሚሊየን የአሜሪካ ዶላር ገቢ መገኘቱን የቡናና ሻይ ባለስልጣን አስታወቀ፡፡

በበጀት ዓመቱ አምስት ወራት 114 ሺህ 335 ነጥብ 63 ቶን የቡና ሻይና ቅመማ ቅመም ምርት በመላክ 367 ነጥብ 56 ሚሊየን የአሜሪካ ዶላር ገቢ ለማግኘት ታቅዶ÷ 138 ሺህ 552 ነጥብ 16 ቶን ወይም 121 በመቶ በመላክ 525 ነጥብ 6 ሚሊየን የአሜሪካ ዶላር ወይም 143 በመቶ ገቢ ተገኝቷል፡፡

አፈጻጸሙ ባለፈው በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ከተላከው ጋር ሲነጻጸር በመጠን 51 ሺህ 298 ነጥብ 87 ቶን ወይም 58 ነጥብ 79 በመቶ በገቢ ደግሞ 244 ነጥብ 50 ሚሊየን ዶላር ወይም 86 ነጥብ 98 በመቶ ጭማሪ ተመዝግቧል መባሉን ከቡናና ሻይ ባለስልጣን ያገኘነው መረጃ ያመላክታል፡፡

የቡና አፈጻጸም በአምስት ወራት ውስጥ 108 ሺህ 35 ነጥብ 70 ቶን ቡና በመላክ 358 ነጥብ 81 ሚሊየን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ለማግኘት ታቅዶ 133 ሺህ 113 ነጥብ 74 ቶን በመላክ 515 ነጥብ 8 ሚሊየን የአሜርካን ዶላር ገቢ ተገኝቷል፡፡

ከባለፈው በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር በመጠን 51 ሺህ 546 ነጥብ 65 ቶን እና በገቢ ደግሞ የ 240 ነጥብ 81 ሚሊየን ዶላር ጭማሪ ታይቶበታል ተብሏል፡፡

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://www.fanabc.com/በ5-ወራት-ከቡና-ሻይና-ቅመማ-ቅመም-ምርት-ኤክ/

## ከአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ምርት የወጪ ንግድ 203 ሚሊየን ዶላር ገቢ ተገኘ

በተያዝነው በጀት ዓመት የመጀመሪያው 5 ወራት ከአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ምርት የወጪ ንግድ 203 ሚሊየን የአሜሪካ ዶላር ገቢ መገኘቱን የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

በ5 ወራት ውስጥ ከአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ምርት 215 ሚሊየን ዶላር ገቢ ለማግኘት ታቅዶ ነው 203 ሚልየን ዶላር ወይም የእቅዱን 94 በመቶ ማግኘት የተቻለው፡፡

ይህም ከባለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወራት ክንውን ጋር ሲነፃፀር የ45 ነጥብ 85 ሚሊየን ዶላር ወይም የ29 ነጥብ 21 በመቶ ብልጫ ማሳየቱን የኢንዱስትሪ ሚኒስትሩ አቶ መላኩ አለበል በማህበራዊ ትስስር ገፃቸው ላይ ባሰፈሩት ፅሁፍ አስታውቀዋል፡፡

ለችግር ሳንበገር ኢትዮጵያን ከድህነት ለማውጣት መስራት የህልውና ትግላችን አካል ነውም ብለዋል ሚኒስትሩ፡፡

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://www.fanabc.com/በ5-ወራት-ከአምራች-ኢንዱስትሪ-ዘርፍ-ምርት/

## የኢትዮጵያ ጥራት ሽልማት ድርጅት ከሜድሮክ ኢንቨስትመንት ግሩፕ ጋር የውል ስምምነት አደረገ




ሜድሮክ ኢንቨስትመንት ግሩፕ በስሩ ያሉትን ድርጅቶች ጥራትን መሰረት አድርጎ ከመስራት አንፃር የኢትዮጵያ ጥራት ሽልማት ድርጅት በትኩረት እንዲመዝንለትና ወደ ለውጥ ጎዳና ለማሳደግ ያለመ ስምምነት መሆኑን የግሩፑ ማኒፋክቸሪንግ ዘርፍ አቅም ግንባታና ሲስተም ማኔጅመንት ዳይሬክተር ቴዎድሮስ ተሰማ ገልፀዋል፡፡

አገርን ለኪሳራ የሚዳርገውና ዓለም ዐቀፍ ተወዳዳሪነትን የሚቀንሰው ጥራትን ካለመጠበቅ መሆኑን የገለጹት ዳይሬክተሩ ጥራት ላይ ተመርኩዞ መስራት ለአገር እድገት ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንዳለው ተናግረዋል።

ዓለም ዐቀፍ ተፅእኖን ለመመከትና ኢኮኖሚን ለማሳደግ ድርጅቶች ጥራትን ዋነኛ መንገድ አድርገው መስራት እንዳለባቸው የኢትዮጵያ ጥራት ሽልማት ድርጅት ዋና ስራ አስፈፃሚ ቴዎድሮስ መብራቱ አሳስበዋል፡፡

ኢትዮጵያ በዓለም ዐቀፍ ደረጃ የራሷ የሆነ በጥራት የምትታወቅበት ምርት እንዲኖራት ጥራትን መሰረት ያደረገ አሰራርን መከተል ይገባልም ተብሏል፡፡

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://waltainfo.com/am/የኢትዮጵያ-ጥራት-ሽልማት-ድርጅት-ከሜድሮ/

## የተቀናጀ የጭነት አገልግሎት ማስተዳደሪያ የትራንስፖርት ሥርዓት ወደ ዲጂታል ተቀየረ




ከዚህ ቀደም በነበረው የፌዴራል ትራንስፖርት ባለሥልጣንና በሌሎች የትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪ መሥሪያ ቤቶች ሲሰጡ የነበሩ አምስት የማስተዳደሪያ ሥርዓት አገልግሎቶች፣ ከታኅሳስ 22 ቀን 2014 ዓ.ም. ጀምሮ ‹‹የተቀናጀ የጭነት ማስተዳደሪያ ትራንስፖርት ሥርዓት›› የሚል ስያሜ በተሰጠው የዲጂታል አገልግሎት ተለውጠዋል፡፡

የቀረበው አገልግሎት ሙሉ ለሙሉ በኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴርና ከዚህ ቀደም ተጠሪ ተቋሙ በነበረው የቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ኢንስቲትዩት ባለሙያዎች አማካይነት ተቀርፆ፣ የተቀናጀ የጭነት ትራንስፖርት ማስተዳደሪያ ሥርዓት እንደሆነ ተገልጿል።

በትራንስፖርት ዘርፍ መሰማራት የሚፈልጉ ግለሰቦችና ባለሀብቶች አዲስ የትራንስፖርት ብቃት ማረጋገጫ፣ ዓመታዊ የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ዕድሳት፣ የአዲስ ተሽከርካሪዎች ምዝገባ፣ የተሽከርካሪ ዝውውር፣ ወደ ጎረቤት አገር የንግድ ትራንስፖርት አገልግሎት ለሚሰጡ አሽከርካሪዎችና ረዳቶች የድንበር ተሻጋሪ መታወቂያ ማውጣት፣ ማደስና ምትክ መስጠት አገልግሎቶች በበይነ መረብ ሥርዓቱ መስጠት ጀምረዋል፡፡

ተገልጋዮች ያላቸውን አስፈላጊ ሰነዶች ስካን በማድረግ አገልግሎቱን በቀላሉ መጠቀም የሚችሉ ሲሆን፣ የተቀናጀ አገልግሎቱን ለማበልፀግ አንድ ዓመት ተኩል የፈጀ ጊዜ ጠይቋል፡፡

በ2013 ዓ.ም. ብቻ 72,000 ለሚሆኑ ድንበር ተሻጋሪ አሽከርካሪዎችና ረዳቶች ወደ ጎረቤት አገር እንዲገቡ የሚያስችላቸውን መታወቂያ ዕድሳትና ፈቃድ ማግኘታቸውን፣ ይህ አገልግሎት ከዚህ በኋላ ሙሉ በሙሉ ወደ ዲጂታል እንደሚቀየር ተገልጿል፡፡

አገልግሎቱ ታኅሳስ 22 ቀን 2014 ዓ.ም. በሸራተን አዲስ ሆቴል ይፋ በተደረገበት መድረክ የተገኙት የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስትር ወ/ሮ ዳግማዊት ሞገስ፣ የተቀናጀ የጭነት ትራንስፖርት ማስተዳደሪያ ሥርዓቱ በደረቅና ፍሳሽ ማመላለሻ ትራንስፖርት ዘርፍ የሚታዩ ችግሮችን ትርጉም ባለው መንገድ የሚቀይር እንደሆነ አስታውቀዋል።

‹‹የትራንስፖርት ዘርፉ ዘመናዊ፣ ብቁና ቀልጣፋ እንዲሆን እየሠራን ነው፤›› ያሉት ሚኒስትሯ፣ ይፋ የተደረገው ሥርዓት ቀልጣፋና ዘመናዊ የጭነት አገልግሎት የሚሰጡ ኦፕሬተሮችን ለማፍራት ያግዛል ብለዋል።

ወ/ሮ ዳግማዊት እንደገለጹት የኢትዮጵያ የገቢና ወጪ ንግድ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ የመጣ ሲሆን፣ የገቢና ወጪ ጭነቶችን በማጓጓዝ ረገድ የተሽከርካሪዎች ድርሻ 90 በመቶ በላይ ሲሆን ቀሪው የባቡርና ሌሎች የሎጂስቲክስ አማራጮች ናቸው፡፡

በትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ የእሴት ሰንሰለት ውስጥ ያሉትን ችግሮች በአሠራር፣ በብቁ የሰው ኃይል፣ በአደረጃጀትና በቴክኖሎጂ መቅረፍ ከተቻለ ኢትዮጵያን የአፍሪካ የሎጂስቲክስ ማዕከል ማድረግ ይቻላል ያሉት በመድረኩ የተገኙት የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር በለጠ ሞላ (ዶ/ር) ናቸው፡፡

የብራይት ድንበር ተሻጋሪ ደረጃ አንድ የደረቅ ጭነት ማመላለሻ ባለንብረቶች ማኅበር ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ሲሳይ ንጉሴ ለሪፖርተር እንዳስታወቁት፣ ይፋ የተደረገው የተቀናጀ የትራንስፖርት ቴክኖሎጂ የትራንስፖርቱ ዘርፍ አገልግሎቶች ዘመናዊ በሆነ መንገድ እንዲሰጡ የሚያስችል ነው፡፡

ከዚህ ቀደም የተቀናጀ ትራንስፖርት አገልግሎቶችን ለማግኘት ውጣ ውረዶች እንደነበሩ፣ ይህም ዘርፉ ላይ ከቴክኖሎጂ ጋር የተገናኙ ሥራዎች በስፋት ባለመስረፃቸው የተነሳ መሆኑን፣ ከአደረጃጀት የተነሳ አገልግሎቱን በሚያገኙ አካላት ዘንድ ቅሬታዎች እንደነበሩ ያስታወቁት አቶ ሲሳይ፣ ነገር ግን ይፋ የተደረገው አዲስ ሥርዓት ከመተግበሩ በፊት ከዚህ ቀደም የተለያዩ ውይይቶችና አስተያየቶች እንደተደረጉ አስረድተዋል፡፡

የትራንስፖርት አገልግሎት አቅራቢ ድርጅቶች ከሚያገኟቸው ወሳኝ አገልግሎቶች መካከል የጂቡቲ መግቢያና፣ የጂቡቲ መግቢያ የተሽከርካሪዎችና አሽከርካሪዎች ፈቃድ ይገኝበታል፡፡ እንዲሁም በዚህ ወቅት በፈረሰው የትራንስፖርት ባለሥልጣን መሥርያ ቤት በኩል ሲሰጡ የነበሩ የዕድሳት ፈቃድ ይጠቀሳል፡፡ እነዚህ አገልግሎት በአካል በመቅረብ የሚሰጡ አገልግሎቶች እንደ መሆናቸው መጠን፣ ቢሮክራሲውን ሰብሮ ገብቶ ለ24 ሰዓታት የሚሰጠውን አገልግሎት ማስተዳደር የራሱ የሆኑ ፈተናዎች ነበሩት፡፡ በተለይም በሳምንቱ የመጨረሻ ቀናት ለዓብነትም ዓርብ ከቀትር በኋላ ወደ ውጭ የሚሄድ ጭነት ቢኖር፣ እስከ ሰኞ ድረስ አገልግሎቱን ለማግኘት መጠበቅ ግድ ይል ነበር፡፡ ሆኖም በኦንላይን ለ24 ሰዓታት የሚሰጥ አገልግሎት መቅረቡ ከሰው ንክኪ ነፃ አገልግሎት ለማግኘት የሚያስችል እንደሆነ ዋና ሥራ አስኪያጁ አስረድተዋል፡፡

በዚህ ወቅት 98 የድንበር ተሻጋሪ የንግድ ጭነት ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ ኦፕሬተሮች፣ እንዲሁም ከ12,700 በላይ የከባድ ጭነት ተሽከርካሪዎች በትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ ሚኒስቴር በማኅበርና በድርጅት ዘርፍ ተሰማርተው አገልግሎት እየሰጡ እንደሚገኙ፣ እንዲሁም የፈሳሽ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ ከ200 በላይ ትራንስፖርተሮችና 3,500 የሚጠጉ የፍሳሽ ማመላለሻ ከባድ የጭነት ተሽከርካሪዎችም መኖራቸው ታውቋል፡፡

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://ethiopianreporter.com/index.php/article/24256

## ብሔራዊ ባንክ የመጀመርያውን የክፍያ ሥርዓት ኦፕሬተር ፈቃድ ሰጠ

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የመጀመርያውን የክፍያ ሥርዓት ኦፕሬተርነትና የጌትዌይ አገልግሎት አቅራቢነት ፈቃድ፣ ለአሪፍፔይ ዲጂታል ቴክኖሎጂ ድርጅት ሰጠ፡፡ በብሔራዊ ባንክ የክፍያ ሥርዓትና ሴትልመንት ዳይሬክተር ወ/ሮ ማርታ ኃይለ ማርያም ለሪፖርተር እንዳረጋገጡት፣ ብሔራዊ ባንክ የብሔራዊ ዲጂታል ፔይመንት ስትራቴጂና መመርያ ካወጣበት ካለፈው ዓመት አንስቶ፣ በርካታ የቴክኖሎጂ አቅራቢ ድርጅቶች ፈቃድ ለማግኘት አመልክተዋል።

መመርያውን መሠረት በማድረግ ባንኩ የክፍያ ሥርዓት ኦፕሬተርነትና የጌትዌይ አገልግሎት አቅራቢነትን ፈቃድ ለአሪፍፔይ ዲጂታል ቴክኖሎጂ መስጠቱን፣ በሞባይል ገንዘብ አገልግሎት ደግሞ ለኢትዮ ቴሌኮም የቴሌ ብር አገልግሎት እንዲሰጥ በተጠናቀቀው ዓመት መፈቀዱ ተገልጿል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በቅርቡ ሌሎች ድርጅቶችም እንደ አሪፍፔይ የዲጂታል ክፍያ አግልግሎቶችን እንዲሰጡ የሚያስችላቸው ፈቃድ እንደሚሰጣቸው ወ/ሮ ማርታ አስታውቀዋል፡፡

የአሪፍፔይ መሥራችና ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ሀብታሙ ታደሰ ለሪፖርተር እንደገለጹት፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ለአሪፍፔይ ሁለት የዲጂታል ክፍያ ሥርዓት አገልግሎቶችን እንዲያቀርብ የመጀመርያ ነው የተባለለትን ፈቃድ ሰጥቷል።

እንደ አቶ ሀብታሙ ገለጻ፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ይፋ ያደረገውን የብሔራዊ ዲጂታል ፔይመንት ስትራቴጂና መመርያ መሠረት በማድረግ ደርጅቱ ፈቃዱን ለማግኘት ከአሥር ወራት በላይ ምላሽ ሲጠብቅ ቆይቷል፡፡

ድርጅቱ ለመጀመርያ ጊዜ ፈቃድ ሲጠይቅ፣ በመመርያው ላይ የተቀመጡትን ቅድመ ሁኔታዎች በዝርዝር ማሟላት እንደነበረበት ዋና ሥራ አስፈጻሚው ገልጸዋል፡፡

ካፒታል ማሟላት የሚለው የመጀመርያው ቅድመ ሁኔታ ሲሆን፣ ከዚያ ውጪ ደግሞ ኢንቨስት የሚያደርጉት ሰዎች ግዴታ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ሊሆኑ ይገባል የሚለው ነው፡፡ በሌላ በኩል ከፋይናንስ ጋር በተገናኘ ያለውን አሠራር ኅብረተሰቡ ያውቀው እንደሆነ፣ ከፋይናንስ ወንጀል ጋር በተገናኘ ያለውን የድርጅቱን የቀደመ እንቅስቃሴ መመልከት ሌላው የሚታይ ጉዳይ መሆኑ ተጠቁሟል፡፡

ከዚህም በተጨማሪም የድርጅቱን ቢዝነስ ዕቅድ ማስገምገም ሌላው በመመርያው ላይ የተቀመጠ መሥፈርት ነው፡፡ ዘርፉ አዲስ እንደ መሆኑ የሚቀጥራቸውን ሰዎችን እንዴት ነው ብቁ ማድረግ የሚቻለው የሚለው ሌላው ሒደት እንደሆነ ተገልጿል፡፡

አቶ ሀብታሙ እንዳብራሩት፣ በመመርያው ውስጥ ከሦስት እስከ አራት የሚደርሱ የክፍያ ሥርዓት ኦፕሬተርነት አማራጭ ፈቃዶች አሉ። አንድ ድርጅት ማግኘት የፈለገው የዋሌት ወይም የሞባይል ገንዘብ አገልግሎት ከሆነ፣ እስከ 50 ሚሊዮን ብር የሚደርስ ዝቅተኛ የተከፈለ ካፒታል መጠን ሊኖረው ይገባል፡፡ ከዚህ ውስጥ አሪፍፔይ የተሰጠው ፈቃድ የክፍያ ሥርዓት ኦፕሬተርነትና የጌትዌይ አገልግሎት አቅራቢነት አገልግሎቶችን ለመስጠት ነው፡፡ ይህም የፖስ ማሽኖችን የሚተካ ሲስተምና የኦንላይን ቢዝነሶችንና በቤት ውስጥ የሚከናወኑ ግብይቶችን በኤሌክትሮኒክ ክፍያቸውን የሚሳለጥበትን አገልግሎት፣ ወይም በሌላ አገላለጽ የኦንላይን ሱቆች ክፍያን ማከናወን የሚቻልባቸው ሲስተሞች ናቸው፡፡

አቶ ሀብታሙ አሪፍፔይ የክፍያ ሥርዓት ኦፕሬተር ፈቃድና የክፍያ ጌትዌይ ኦፕሬተር ፈቃድ እንዳገኘ ገልጸው፣ የሁለቱን አገልግሎቶች ፈቃድ ለማግኘት የሚጠበቀው ዝቅተኛ የተከፈለ ካፒታል ብር መጠን በአጠቃላይ 13 ሚሊዮን ብር ቢሆንም፣ እንደ እሳቸው እምነት ይህ የገንዘብ መጠን አገልግሎቱን ለመተግበር በቂ ሊሆን አይችልም። ይህንን ግምት ውስጥ በማስገባት 42 ባለአክሲዮኖች ያሉት አሪፍፔይ ኩባንያ፣ በ140 ሚሊዮን ብር የተከፈለ ካፒታል እንደተቋቋመ አስታውቀዋል።

አሪፍፔይ ዲጂታል ዋሌት ቢዝነስን ለመሥራት ሳይሆ ካርድ ፕሮሰስ ወደ ማድረግ አገልግሎት የሚገባ እንደሆነ ያስታወቁት አቶ ሀብታሙ፣ ይህም ኤቲኤም ካርድን በመጠቀም በኦንላይንም ሆነ በአካል የሚፈጸሙ ክፍያዎችን ለማስተናገድ የሚያስችል አገልግሎት ነው፡፡

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://ethiopianreporter.com/index.php/article/24175

## ከ147 ነጥብ 3 ቢሊየን ብር ገቢ ተሰበሰበ

በአምስት ወራት ውስጥ 147 ነጥብ 3 ቢሊየን ብር ገቢ መሰብሰብ መቻሉን የገቢዎች ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

ሚኒስትሩ አቶ ላቀ አያሌው በማህበራዊ ትስስር ገፃቸው፥ ባለፉት አምስት ወራት ውስጥ የኮሮና ወረርሽኝን፣ አገራዊ የፀጥታና መሰል ተግዳሮቶችን በመቋቋም 147 ነጥብ 3 ቢሊየን ብር ገቢ መሰብሰብ ተችሏል ብለዋል።

በዚህም የእቅዱን 92 ነጥብ 69 በመቶ ማሳካት መቻሉ ተገልጿል፡፡

ገቢው ከ2013 በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወራት ጋር ሲነፃፀርም የ20 ነጥብ 6 ቢሊየን ብር ወይም 16 ነጥብ 27 በመቶ ዕድገት አሳይቷል ተብሏል፡፡

ገቢው የተሰበሰበው ከሀገር ውስጥ ታክስና ከውጭ ንግድ ቀረጥና ታክስ መሆኑ ታውቋል፡፡

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://www.fanabc.com/በአምስት-ወራት-ውስጥ-147-ነጥብ-3-ቢሊየን-ብር/

## ከማዕድን የወጪ ንግድ 241 ሚሊየን ዶላር ገቢ ተገኘ

ባለፉት አምስት ወራት ከማዕድን የወጪ ንግድ በተለይም ከወርቅ 241 ሚሊየን ዶላር ገቢ ማግኘት መቻሉን የማዕድን ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

የማዕድን ሚኒስትሩ ኢንጂነር ታከለ ዑማ በማህበራ ትስስር ገፃቸው “አሁን ካለንበት ሀገራዊ ሁኔታ በተለይም በማዕድን አካባቢዎች የሚከሰቱ የፀጥታ ችግሮችን ተቋቁመን የተመዘገው ገቢ አበረታች ነው” ብለዋል።

ያሉ ችግሮችን እየፈታን እና እየሄድንበት ያለውን መንገድ አጠንክረን ከቀጠልን የማእድን ምርታችን በተለይም የኢኮኖሚያችን ማገር መሆን እንደሚችል እየታየ ያለው ውጤት ማሳያ ነው ሲሉም በፅሁፋቸው አስፍረዋል፡

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://www.fanabc.com/በባለፉት-አምስት-ወራት-ከማዕድን-የወጪ-ንግ/

# በኢትዮጵያ መዋዕለ ንዋያቸውን ማፍሰስ የሚፈልጉ ዳያስፖራዎችን የሚያበረታታ ፎረም ተዘጋጀ




የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን እና የአዲስ አበባ ኢንቨስትመንት ቢሮ ጋር በመሆን በሀገሪቱ መዋዕለ ንዋያቸውን ማፍሰስ የሚፈልጉ ዳያስፖራ ባለሀብቶችን የሚያበረታታ እና ግንዛቤ የሚያሳድግ ፎረም አዘጋጁ።

ሁለቱ ተቋማት በጋራ በሠጡት መግለጫ ፎረሙ ጥር 3 ስራ የሚጀምር ሲሆን፥ ጥር 6 ይጠናቀቃል ተብሏል፡፡

ፎረሙ ጥር 3 በይፋዊ የመክፈቻ ሥነ-ሥርዓት እንደሚጀመር እና በቀጣይ ቀናትም የተለያዩ መርሃ ግብሮች እንደሚኖሩት ነው ኮሚሽኑ የገለጸው፡፡

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን፥ ኢትዮጵያ ውስጥ መዋዕለ ንዋያቸውን የማፍሰስ ዕቅድ ያላቸው ዳያስፖራ ባለሐብቶች በፎረሙ እንዲሳተፉ እና ከኢንቨስትመንት ማኅበረሰቡ፣ ከኮሚሽኑ የፌዴራል እና የክልል እንዲሁም የከተማ አሥተዳደር ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ጋር እንዲመክሩ ብሎም የኢንቨስትመንት አማራጮችን እንዲመለከቱ ነው ጥሪ ያቀረበው፡፡

በኢንቨስትመንት መሰማራት እና በዕድሉ መጠቀም የሚፈልጉ ባለሐብቶች investethio.com የሚለውን የኮሚሽኑን ድረ ገጽ መመልከት እንደሚችሉም ተጠቁሟል፡፡

የልምድ ልውውጥ እና የኢንዱስትሪ ፓርኮች ጉብኝት እንደሚኖር የተገለጸ ሲሆን፥ ይህም ዳያስፖራው በኢትዮጵያ ያለውን የኢንቨስትመንት አማራጭ እና አቅሙን እንዲያውቅ እና መዋዕለ ንዋዩን እንዲያፈስ ያስችለዋል ተብሏል፡፡

ዳያስፖራው በሚያገኛቸው አጋጣሚዎችም የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት አምባሳደር ሆኖ ለዓለም አቀፉ ማህበረሰብ እንዲያስተዋውቅ ግንዛቤ የሚሰጥ ጉብኝት እንደሚሆን ኮሚሽነር ለሊሴ ነሜ ገልጸዋል።

በፎረሙ ሰባት የሚደርሱ ሚኒስትር መሥሪያ ቤቶችያሏቸውን የኢንቨስትመንት አማራጮች እንደሚያቀርቡም ተመላክቷል።

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://www.fanabc.com/በኢትዮጵያ-መዋዕለ-ንዋያቸውን-ማፍሰስ-የ/

# ሆቴሎች የብድር መክፈያ ጊዜ ለአምስት ዓመት እንዲራዘምላቸው ጥያቄ አቀረቡ

በኮሮና ቫይረስ ምክንያት በገበያ መቀዛቀዝ ገቢያቸው የተጎዳ ሆቴሎችን ለመደገፍ የተሰጠው ብድር መክፈያ ጊዜ ለአምስት ዓመታት እንዲራዘም ለብሔራዊ ባንክ ማመልከቻ ማስገባቱን፣ የሆቴሎችና መሰል አገልግሎቶች አሠሪዎች ፌዴሬሽን አስታወቀ፡፡

የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ መከሰቱን ተከትሎ ሆቴሎች በቀጥታ ተጎጂ በመሆናቸው፣ ችግሩን መቋቋም እንዲችሉና ሠራተኞቻቸውን እንዳያሰናብቱ ለብሔራዊ ባንክ ባቀረቡት የ6.6 ቢሊዮን ብር የብድር ጥያቄ መሠረት፣ ባንኮች በኮሮና ቫይረስ ለተጎዱ 1,400 ሆቴሎች 3.3 ቢሊዮን ብር ብድር እንዲያበድሩ መደረጉ ይታወሳል፡፡

በአምስት በመቶ ወለድ የተሰጠው ይህ ብድር፣ የኮሮና ወረርሽኝ ለአንድ ዓመት እንደሚቆይ ታሳቢ ተደርጎ የተሰጠ ሲሆን፣ የመክፈያ ጊዜ ሲደርስ ብድሩ እንዲራዘም ተጠይቆ ለስድስት ወራት ተራዝሞ ነበር፡፡ ነገር ግን ሆቴሎች ከፍተኛ የጥሬ ገንዘብ እጥረት ያለባቸው በመሆኑ፣ ከመደበኛ ብድራቸው በተጨማሪ በኮሮና ወቅት የተሰጣቸውን ብድር የመክፈል አቅማቸው መዳከሙን፣ የሆቴሎችና መሰል አገልግሎቶች አሠሪዎች ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት ፍትሕ ወልደሰንበት (ዶ/ር) ለሪፖርተር ገልጸዋል፡፡

በዚህም መሠረት ሆቴሎች በኮሮናና በጦርነቱ በደረሰባቸው የሥራ መቀዛቀዝ ምክንያት የመክፈል አቅም ስለሌላቸው፣ ብድሩ ለአምስት ዓመታት እንዲራዘም ለብሔራዊ ባንክ ማመልከቻ ማስገባታቸውን ተናግረዋል፡፡

ዘርፉ ከኮሮና በተጨማሪ በጦርነቱ ምክንያት በቂ የማገገሚያ ዕድል ባለማግኘቱ በወረርሽኙ ወቅት ከተሰጠው ብድር በተጨማሪ የበርካታ ሆቴሎች የመደበኛ ብድር መመለሻ ጊዜ በመድረሱ አጣብቂኝ ውስጥ መሆናቸውን በመግለጽ፣ የመደበኛ ብድሮች መክፈያ ጊዜም እንዲራዘም መጠየቃቸውን አስረድተዋል፡፡

የጎልደን ቱሊፕ ሆቴል ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ደረጀ ቦጋለ የሆቴላቸው ሥራ አሁንም ቀዝቃዛ መሆኑንና የመኝታ ክፍሎች እንግዶችን የማስተናገድ መጠን (occupancy rate) ከ20 በመቶ በታች እንደሆነ ገልጸው፣ በጥሬ ገንዘብ እጥረት ምክንያት ለሠራተኞች ደመወዝ ለመክፈልም መቸገራቸውን ገልጸዋል፡፡

‹‹ለአገር ውስጥ ደንበኞች የ50 በመቶ የዋጋ ቅናሽ በማድረግ ገበያውን ለማነቃቃት እንደ መፍትሔ ለመጠቀም ብንሞክርም፣ አሁንም ለውጥ ሊያመጣ አልቻለም፤›› ካሉ በኋላ፣ ‹‹በኮሮና ምክንያት የወሰድነውን ብድር መክፈያ ጊዜ ሊራዘምልን ይገባል፤›› ብለዋል፡፡

የብድር ማራዘሚያ ጊዜውን በተመለከተ የብሔራዊ ባንክ ምክትል ገዥ አቶ ፍቃዱ ደገፉ፣ የብድር መክፈያ ጊዜውን ለማራዘም ሆቴሎቹ የደረሰባቸውን ጉዳትና ያሉበትን አቅም መረጃ እየታየ ነው ብለዋል፡፡ ‹‹ብድሩ የሚራዘምላቸው ሆቴሎችንና ለምን ያህል ጊዜ እንደሚራዘም›/ ለመለየት መረጃ በመሰብሰብ ጥናት እያደረግን ነው፤›› ሲሉ አቶ ፍቃዱ ለሪፖርተር ገልጸዋል፡፡

በጦርነቱ ሳቢያ የቱሪዝም ፍሰት በመቀነሱ የሆቴል ዘርፉ ጉዳት ደርሶበታል ያሉት ፍትሕ (ዶ/ር)፣ ‹‹የደረሰውን ጉዳት በገንዘብ ለመተመን በመጠናት ላይ መሆኑን አንስተው፣ የደረሰውን ጉዳት ለማካካስ ወደ አገር ቤት እንዲመጡ ጥሪ የተደረገላቸው ዳያስፖራዎች ሲመጡ፣ በሆቴልና ቱሪዝም ዘርፉ ላይ ከፍተኛ መነቃቃት ይፈጥራል ብለን እንጠብቃለን፤›› ብለዋል፡፡

እንግዶቹ ደጋግመው እንዲመጡ የሚያደርግ አገልግሎት መስጠት እንደሚያስፈልግ ገልጸው፣ በአንድ ጊዜ ከሚገኘው ገንዘብ በላይ የሚፈጠረው መልካም ገጽታ ደጋግመው እንዲመጡ የሚያደርግ እንደሚሆንም ጠቁመዋል፡፡

‹‹እነዚህ ሁሉ ሰዎች ነገ የእኛ አምባሳደሮች ይሆናሉ፣ ለዚህም ከታኅሳስ 23 ቀን 2014 ዓ.ም. ጀምሮ ከ30 በመቶ የዋጋ ቅናሽ በተጨማሪ ቆይታቸውን እንዲያራዝሙ የሚያደርጉ አገልግሎቶችን ለማቅረብ ዝግጅት ተደርጓል፤›› ብለዋል፡፡

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://ethiopianreporter.com/index.php/article/24246

# የመኪና ታርጋ ለማውጣት ተቀምጦ የነበረው ቅድመ ሁኔታ እንዲቀር ተደረገ

የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ አዳዲስ ተሽከርካሪዎች ሰሌዳ (ታርጋ) ለማግኘት የፍጥነት መገደቢያ መሣሪያ ማስገጠምና በተቀመጠው ስታንዳርድ መሠረት መገጠሙን የሚያረጋግጥ ቅድመ መስፈርት ማስረጃ የማቅረብ ግዴታ በጊዜያዊነት መነሳቱን ገለጸ፡፡

ሚኒስቴሩ ይኼንን ቅድመ ሁኔታ ያነሳው የፍጥነት መገደቢያ መሣሪያ አገጣጠም ላይ ያሉ ችግሮችን የሚፈታ ጥናት ማድረግ በማስፈለጉ መሆኑን አስታውቋል፡፡

ከተፈቀደው የፍጥነት ወሰን በላይ በማሽከርከር የሚከሰት የትራፊክ አደጋ ቁጥር መጨመሩን ተከትሎ፣ በ2011 ዓ.ም. የተሽከርካሪዎች የፍጥነት መገደቢያ መሣሪያ መግጠምና ማስተዳደርን የተመለከተ መመርያ የወጣ ሲሆን፣ ከመመርያው መውጣት በኋላ ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ አዳዲስ ተሽከርካሪዎች፣ የመኪና ታርጋ ከማግኘታቸው በፊት የፍጥነት መገደቢያ መሣሪያን ማስገጠማቸውን የማረጋገጥ ግዴታ ነበረባቸው፡፡

ሪፖርተር ያነጋገራቸው የሚኒስቴሩ ከፍተኛ የሥራ ኃላፊ አቶ አብዱልበር ሸምሱ፣ ሚኒስቴሩ ይኼንን ውሳኔ ያሳለፈው ቅድመ ሁኔታው አዲስ ተሽከርካሪ የሚያስገቡ ባለንብረቶች ላይ ያስከተለውን ‹‹አላስፈላጊ›› ቢሮክራሲን ለመቀነስ መሆኑን አስታውቀዋል፡፡ ኃላፊው ይኼንን የተመለከተ የአሠራር ማሻሻያ ለማድረግ ጥናት እየተደረገ መሆኑ የገለጹ ሲሆን፣ ከጥናቱ መጠናቀቅ በኋላ አሠራሩ ሙሉ ለሙሉ ወደነበረበት ሊመለስ አልያም በተሻለ መንገድ መተግበር ሊቀጥል እንደሚችል ተናግረዋል፡፡

በ2011 ዓ.ም. በወጣው መመርያ መሠረት የፍጥነት መገደቢያው የሚገጠምላቸው ተሽከርካሪዎች የምርት ዘመናቸው እ.ኤ.አ. ከ2000 እና ከዚያ በኋላ የተመረቱ ተሽከርካሪዎች ናቸው። የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር እያደረገ ባለው ጥናት የፍጥነት መገደቢያ መሣሪያ ሊገጠምባቸው የሚገባቸውን ተሽከርካሪዎች ዓይነትን ለመለየት እንዳሰበ ገልጿል፡፡

‹‹መመርያው መሣሪያው ሚገጠምላቸው ተሽከርካሪዎች የምርት ዘመን ላይ ልዩነት ቢያስቀምጥም፣ ማንኛውም ዓይነት ተሽከርካሪ የፍጥነት መገደቢያ መሣሪያ እንዲገጥም ያዛል፤›› ያሉት አቶ አብዱልበር፣ እንደ አገር ሁሉም ተሽከርካሪ ላይ ገጠማ የማድረግ ሥራ ከመሥራት ቅድሚያ የሚሰጣቸውን መለየት እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል፡፡

በዚህም መሠረት አዲሱ አሠራር ተፈጻሚ መሆን ሲጀምር ገጠማው መኪናዎቹ በሚያደርሱት የአደጋ መጠን እንደሚለያቸው ገልጸው ‹‹አደጋን ከመቀነስ አንፃር ሁለት ሰው የሚጭን መኪና ላይ ከመግጠም የሕዝብ ተሽከርካሪ ላይ በቅድሚያ ማድረግ የተሻለ ነው፤›› ብለዋል፡፡

ከዚህም ባሻገር በአተገባበሩ ላይ ብልሹ አሠራርና የመልካም አስተዳደር ችግሮች መታየቱ ተገልጿል፡፡ አቶ አብዱልበር የፍጥነት መገደቢያ መሣሪያ ገጠማው ላይ የሚሳተፉ አካላት ብዙ መሆናቸውን የተናገረው፣ ይኼም ሥራው በተፈለገው መልኩ እየተፈጸመ መሆኑን ለማረጋገጥ የማያስችል ክፍተት እንደፈጠረ አስታውቀዋል፡፡ አሁን እየተደረገ ባለው ጥናት ይኼንን ክፍተት ለመድፈን የታሰበ ሲሆን፣ ጥናቱ ማሻሻያ የሚያስፈልገው ‹‹መመርያው ላይ ነው ወይስ ሒደቱ ላይ የሚለውን ይለያል፤›› ተብሏል፡፡

በሚኒስቴሩ አዲስ ማሻሻያ መሠረት ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ አዳዲስ መኪናዎች፣ የመኪና ታርጋ ለማግኘት ፍጥነት መገደቢያ መሣሪያ ማስገጠም ቅድመ ሁኔታ መሆኑ ለጊዜው ቢቀርም፣ መሣሪያውን ማስገጠም ግን አለመቅረቱ ተገልጿል፡፡ ተሽከርካሪ የሚያስገቡ ባለ ንብረቶች በማንኛውም ጊዜ ተሽከርካሪዎቻቸው ላይ መገደቢያውን ማስገጠም እንዳለባቸው የሚገልጽ የግዴታ ስምምነት መፈረም እንዳለባቸው ታውቋል፡፡ በግዴታ ስምምነቱ መሠረትም ቀጣይ ሚኒስቴሩ የማጣራት ሥራ እንደሚሠራ አቶ አብዱልበር ተናግረዋል፡፡

የፍጥነት መገደቢያ መሣሪያ መግጠም ግዴታ ሆኖ መተግበር የጀመረው ከ2012 ዓ.ም. መጨረሻ ጀምሮ ሲሆን፣ እስካሁን ከ32 ሺሕ በላይ ተሽርካሪዎች የመገደቢያ መሣሪያ እንደተገጠመላቸው ታውቋል፡፡ የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር አሠራሩን ለማሻሻል የሚያደርገውን ጥናት በአንድ ወይም በሁለት ወር ውስጥ ለማጠናቀቅ እየሠራ መሆኑም ተገልጿል፡፡

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://ethiopianreporter.com/index.php/article/24081

ዋና አዘጋጅ፡-
ደበበ አበበ

አዘጋጅ፡-
ዮሴፍ ተሾመ

አድራሻ፡-

ስልክ-፡- +251-115-54-09-93

ፋክስ፡-+251-011-5517699

ድረ-ገጽ፡-
www.ethiopianchamber.com

Facebook:
https://www.facebook.com/EthiopianChamber

Twitter:
https://twitter.com/EthiopiaChamber

Telegram:
t.me/ethiopiachamber

## ECCSA Resource Center

Ethiopian Chamber of Commerce & Sectoral Associations (ECCSA) Resource Center has stated giving service to member. The center is located at the head quarter of ECCSA.

It is a unit dedicated to serve the business community, its members and staffs with a range of timely and cost-effective information services which will enhance the decision-making process and competitiveness of the chamber system management and the business community.

It is also a WTO (World Trade Organization) Reference Center for the private sector, to enable business community to access online trade data and WTO-related documents on a continuous basis, to help identify market niches for the export of their products and services.

The center works on the principle of the 5Rs: providing the Right information to the Right person at the Right time in the Right quantity and Right quality.

The Center's Services

Reference, Resources Loan & Interlibrary Loan Services

Internet & Electronic Resource Services

Support on information searching

Reprographic Service

Advising users on reference materials available in resource center.

Types of Materials in the Center

Books, Periodicals, Journals, Magazines

Audio and Video CD collections

E-Books & Publications

Business & Economic Statistics & Databases

Access to international organization's online information (WTO, ITC, UNCTAD, World Bank, PACCI, WCO, etc.)

For further information:

Ethiopian Chamber of Commerce and Sectoral Associations

ECCSA Resource & WTO Reference Center

Mexico Square, ECCSA Building

Ground Office , Room No. 13/14

Open to public Monday-Friday from 2:30 am to 5:00 pm

Tel: 251-115514005

Mob. 0966038499

Fax: 251-115517699

# የግልግል አገልግሎት



የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት በማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 341/95 አንቀጽ 5(6) መሰረት በንግድ ማህበረሰቡ መካከል የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን እንዲፈታ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡ በዚህም መሰረት አለመግባባቶችን በፈጣን እና ሚስጥራዊነቱ በተጠበቀ ሁኔታ እንዲፈታ ከማድረጉም በላይ ለባለ ጉዳዮች አመቺ እንዲሆን ቅዳሜንም ጨምሮ ዓመቱን ሙሉ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡ በመሆኑን የዚህ አገልግሎት ተጠቃሚ እንድትሆኑ ስንጠይቅ የንግድ ማኅበረሰቡን ለማገልገል ያለንን ቁርጠኝነት በመግለጽ ነዉ፡፡

ለበለጠ መረጃ ፡- ሜክሲኮ አደባባይ በሚገኘዉ የንግድ ምክር ቤት ሕንጻ 1ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 15 በአካል በመቅረብ
ወይም
በስልክ ቁጥር +251 115 311015 በመደወል ማነጋገር ትችላላችሁ፡፡

**የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት**
**የግልግል ማዕከል**